# ክርታታ ኮከቦች



ማዕበል ፈጠን

Scanned with CamScanner




ዋ.ጋ 233.00
$ 20

Scanned with CamScanner

# ከርታታ ኮከቦች

## ማዕበል ፈጠነ

ለአይታም ብቻ በ 09 20 75 92 51-

ኢትዮጵያ ፳፻፲ወ፫ ዓ.ም

ማዕበል ፈጠነ

© መብቱ በረቂቅ ጥበብ የተጠበቀ ነው!!

ቀዳሚ ዕትም ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ከልኤቱ- መስከረም 2014 ዓ.ም

ለአ.አ ወኪል

በ 09 23 97 68 96

ዋና አከፋፋይ "ከርታታ ኮከቦች መጻሕፍት" ባ/ ዳር 09 21 61 44 95





# ፩

ትድመ ታሪክ

ሲነግሡ ዐሥር ዓመት ሲቀራቸው "ወደ አፍሪካ ተመልከቱ። ጥቁር ንጉሥ ይነግሣል። የመስጠት ዓመት ይመጣል።" ሲል የጥቁሮች አፈ-ሊቅ ማርከስ ጋርቬይ ተናገረ። ትንቢቱ ደርሶ ጃንሆይ ነገሡ። በጃማይካዎች ዘንድ መለኮታዊ ፍቅር ተቸራቸው። ዳሩ ምን ይሆናል? የጃማይካ ሰማይ አመፀባቸው።

......

ተከስተ የደብረ ኤልያስ የቅኔ ተማሪ ነበር። ተማሪ ሳለ ከአዲስ አበባ በቀር ያልዞረበት ሀገር የለም። በኋላ አዲስ አበባም መጣ። ቤተ መንግሥት የገባ ቀን በአዲስ አበባ ላይ ውሽንፍር ነፋስ ለቀቀባት። የዝናም መዓት ወረደ። አዲስ አበባ በጕርፍ ተጥለቀለቀች። የነፋሱን አውታር ወደ ኦጋዴን ሲገጩው ወበቅማዋ ሱማሌ ተደገመች። ዋቢ ሸበሌ ከወሰኑ አልፎ የጎዴን ከተማ ሲያስጨንቃት አደረ። ጃንሆይ ይህን ነፋስ ወደ ጃማይካ ሰማይ እንዲልከው ተማጠኑት። ያ ጊዜ በጃማይካ ሰማይ ዝናም ነጥፎ ነበር። ተከስተ በሰላም ተኝቶ አድሮ ሊነጋጋ ሲል የጀማይካን የምድር ወገብ በሐሳብ-ሰማይ

ስለቱ የሁለተኛዋን ሰማይ መስኮት ተራቀቀባት። የረጋውን ደመና በነፋስ አውታር ሲገጩው የጃማይካ ሰማይ በደመና ተከበበች። ሰማዩ ዝናም ቋጠረ። ጃንሆይ ወደ ጃማይካ እንዲያቀኑ ነገራቸው። ሳያወላውሉ ወደ ጃማይካ በረሩ። በዚያች ዕለት በጃማይካ ሰማይ ሥር ዝናሙ እንደ ጉድ ወረደ። ደመናው ሲያገርብብ ቆይቶ ጃንሆይ ከመነሣታቸው ቀደም ብሎ ቢያጥለቀልቀው ጃማይካ ውቅያኖስ ሰበሰች። ጃንሆይ እንደ አምላክ ተቆጠሩ።

ከጃማይካ መልስ ወደ ደቂቀ ተዋነይ ሲወስዳቸው ከመልአከ ሞት መግቻው ሊያምሳቸው ቃል ነበረው። ጃንሆይም ቀሪ ዘመናትን በዚያ ሊያሳልፉ ቃል ገብተውለት ነበር። ምክንያቱ በውል ሳይታወቅ ወደ ጠቢባኑ ዓለም ሲመለስ ዐባይ ሸለቆ ውስጥ ሽፍቶች ቀጥቅጠው ገደሉት። በዚህ የተናደዱ ደቂቀ ተዋነይ ከፊሎቹ በጃንሆይ ዛቱ። ከፊሎቹ ጠቅልለው ወደ ጠቢባኑ ዓለም ተሰደዱ። ሲሰደዱ መኻል ሀገር ያሉ የጥበብ መጻሕፍትን ይዘው ተሰደዱ። ከፊሎቹ ቀለማቸው እንዳይነበብ ልቅም ባለው የብራና ጽሑፍ ሳይ ቀለም እያፈሰሱ ቀይ ቀዩን በቀይ፣ ጥቁር ጥቁሩን በጥቁር ቀለማት አቀለሟቸው። ብራናው በቀለማቱ ተጨማለቀ። የስቋር ኪዳን ምሕረት የጥበብ መጻሕፍትም በጥቁር ቀለም ቀለሙ። የጎንጅ ደብረ ጥበብ መጻሕፍት በቀይ ቀለማት ሲኳሉ





ዐይናቸው ተደረገመ። ይህን ያደረጉ ሊቆች ከሰዉሩ ዓለም ከገቡ በኋላ ምላሳቸውን በራሳቸው ፈቃድ ቆረጡ። ሌሎች የጦር ዕቃቸውን ጭምር ሰለቡ። ይህን ሊያደርጉ የቻሉት ወደ መኻል ሀገር የመመለስ ፍላጎታቸው ጨርሶ እንዲከስም ነበር። ከሰመ። ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያም ጥበብ ከሰመች። ጃንይሆይም ቀስ በቀስ ተስፋ ቢስ ሆኑ። ከተከስተ ሞት በፊት በጥበብ ያምኑ ነበር። ከተከስተ ሞት በኋላ በእድል ብቻ ማመን ጀመሩ። እድል መርታ መርታ መቃብር አወረደቻቸው። ተከስተ ቢኖርላቸው ኑሮ ጥበብ መርታ መርታ ከጠቢባኑ ዓለም ታደርሳቸው ነበር። የሞት መግቻውም በዚያ ይጠብቃቸው ነበር። ያ ሳይሆን ሲቀር ጃንሆይን አፈር በላቸው። ከፊል ጃማይካውያን አምላካቸውን ቀብረው አሁን ድረስ አሉ። ከፊል ጠቢባን ደግሞ አሁን ድረስ የሞት መግቻው በእጃቸው ነው።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)



Scanned with CamScanner

## ፪

ቦሩ ሜዳ -ወሎ

ወሎ ቦሩ ሜዳ አንድ መንደር አለ፡፡ ከዚያ ውስጥ ዐራት ዐይና ሊቅ ነበሩ፡፡ ለቦሩ ሜዳ ሊቃውንት ሁለተኛ ሊቅ ናቸው፡፡ ስማቸው ተፈሪ ሲሆን በሊቅነት ከቀለም ቀንዱ አካለ ወልድ ዘቦሩ ሥላሴ ለጥቀው ይጠቀሳሉ፡፡ አካልዬ ከሞቱ ከብዙ ዓመታት በኋላ ዐራት ዐይናው ተፈሪ ተኳቸው፡፡ ዐራት ዐይናውም በቀለም አያያዙ "ነበልባል" የሆነ ልጅ ወለዱ፡፡ የአብራካቸው ክፋይ ሲሆን በቀለም በኩል ደግሞ ረመጥ ነበር፡፡ የቀለም ረመጥ፡፡ በተፈጥሮው ገራገርና ትሑት ሲሆን በቀለም በኩል ግን ነበልባል ኾነ፡፡ የነበልባል ረመጥ፡፡ ፊደል መቁጠር ሲጀምር "ነበልባል" የሚል ቅጽል ከጓደኞቹ ተሰጥቶት ነበር፡፡ አባቱ ተፈሪ ግን ተቃወሙ፡፡ ልጄ ነበልባል መባል የለበትም፡፡ 'ከዐይን ውስጥ ይገባብኛል' ሲሉ አጥብቀው በመቃወማቸው ነበልባል ቀርቶ ቀለሙ ተባለ፡፡ ቀለሙ ተፈሪ!!

ያ ሊቅ ቀለሙ ተፈሪ ይባላል!!

ቀለሙ ከእሱ በፊት በቦሩ ሜዳ ፊደል ከቆጠሩ፣ ቅኔ ከቀሰሙ ሊቆች ይለያል፡፡ ከቀለም ቀንድ የተቀዳ ንጹሕ ቀለም ነው፡፡





ጥቁሩን ቀለም ውበት የሚሰጥ ቀለም ነበር-ቀይ ቀለም፡፡ ጥቁሩን ቀለም ውበት የሚሰጥ ቀለም ... 

እስከ ጎንደር ተንከራትቶ ሸንጡን ገትሮ ከተማረ በኋላ የደረሰበት ጠፋ።

የቦሩ ሥላሴ የመጽሐፍ ተማሪዎች ሲገልጹት "ሞተ ወኢተአውቀ መቃብሪሁ ይላሉ። ቢሞትም ቅሉ መቃብሩ አልታወቀም" ማለታቸው ነው። ሞተ ማለት ከሰው ተለየ ማለት ሲሆን መካነ መቃብሩ አልታወቀም ማለት ደግሞ ሌላ ምሥጢር አለው። የቦሩ ሥላሴ ሊቆች እንዳሉት ሞት ማለት ከሰው መለየት ሲሆን፣ ቀለሙ ከአባቱ ከእናቱ፣ ከቦሩ ሥላሴ ሊቃውንት ተለይቷል። ቀለሙ እንደ ወጣ ሲቀር አባቱ ተፈሪ ሰማይ ምድሩ ጠበባቸው። ሌሊት በጨረቃ ነው መሰስ ብሎ የወጣው።

ጓደኞቹ እስከ አማራ ሳይንት ሸኝተውታል። ከዚያ በኋላ ጎጃም እንደተሻገረ ጭምጭታ ነበር። ጭምጭምታውን ተከትሎ አባቱ ተፈሪ ፍለጋ ጀመሩ። ጎጃም ቅኔ ቤት እንደታየ ሲሰሙ ጎጃምን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ በሰማይ በምድር አሥሠው አሥሠው ዱካውን ሲያጡት ወደ ደንቢያ ተሻገሩ። ደንቢያ ውስጥ ስለ ከርታታ ከዋክብት የሚተነትን መጽሐፍ አለ። ያን ለመቀጸል የሄደ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን ወደዚያ ቦታ ብቅ እንዳላለ ተረዱ። ደንቢያን ከአፍ እስከ ጠረፉ ፈትሸው ወደ ጎንደር





ከተማ ዘለቁ። በጎንደርም እንዲሁ እግራቸው እስኪላጥ ሲንከራተቱ ከርመው ፍንጭ አጡ። እየቆዘሙ ወደቦሩ ሜዳ ተመለሱ። ከሚስታቸው ጋር ቤት ዘግተው ለወራት አነቡ። ከወራት በኋላ ሰቆቃው የምር እንዲወጣላቸው የአደባባይ መርዶ አወጁ። በየመንደሩ መርዶ ተለፈፈ። ሀገር ተሰበሰበ። መርዶው ሲጀመር ግን ሬሳ አልነበረም። ባዶ መርዶ ነበር። መርዶው እንዳበቃ አባቱ ለወገናቸው ያስተላለፉት የኀዘን መልእክት ይህ ነበር።

"እንደ ሀገር እኔም የአብነት መምህር ነኝ። ቦሩ ሥላሴ በፍካሬ ታግያለሁ። በደሳሳዋ ጎጆ ስላደግሁ የቆሎ ተማሪን ጠባይ አውቀዋለሁ። የቆሎ ተማሪ የሚሞትበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለበእንተ ማርያም እንደሄደ በተለከፈ ውሻ ተነክሶ ሆዱ ውስጥ የውሻ ቡችላ ፈልቆበት እንደውሻ "ኡ.. ኡ.. ኡ.." እያለ የሚሞት ብኩን ተማሪ አለ። ቀለብ ለመሰብሰብ ቆላ ለቆላ ሲንከራተት የቆላ ንዳድ ነድፎ የሚጥለው ጆቢር ተማሪም አይጠፋም። ገሚሱ ደግሞ ለዘመቻ ታፍሶ እንደዘመተ የጥይት ራት የአሞራ ሲሳይ ይሆናል።" ካሉ በኋላ ከመርዶው የተረፈ እንባ ተናንቋቸው ከመናገር ዝም አሉ። የቦሩ ሥላሴ ሊቃውንት አብረው አለቀሱ። የቀለሙ ትዝታ ተቀስቅሶባቸው የእንባ ማዕበል ወሰዳቸው። ተፈሪ በሰው ተደግፈው ቁመው ንግግራቸውን ቀጥለው ነበር።

ዐይናቸውን በመሐረባቸው እስኪጠርጉ ድረስ አንድ ወጣት ሊቅ ተነሣ:: የእሳቸው የመጨረሻ ልጅና የእሱ የበኵር ልጅ የቀለም ጓደኞች ናቸው::

"በእኛም ዘመን ሊቆች ያለቁት በዘመቻ ነበር:: እየታፈሱ ወደሰሜን ዘመቱ:: ከታፈሱት መካከል የቅርብ ጓደኛዬ ናርዶስ ይባል ነበር:: ናርዶስ እንደ ሴት መልከ መልካም ነበር:: በዚህ ዘመንም "ናርዶስ" በአብዛኛው የቆንጆ ሴት ስም እንደሆነ ታውቃላችሁ:: ባለንጀራዬ ናርዶስ ደምግባቱ ቆንጆ ነበር:: ከእኔ ጋር ባንድ ጎጆ ሁለት ዓመት አሳልፈናል:: መጀመሪያ ቅኔ ያስቀጸልሁት እኔ ራሴ ነኝ:: ሰምና ወርቅ እስኪያውቅ ድረስ እንቅልፍ አልነበረውም:: ሌሊት በሕልሙ ሳይቀር ቀለም ያጠናል:: በመንፈቅ ተቀኘ:: በሁለት ዓመቱ ጫፍ የወጣ ሊቅ ሆነ:: ሊቅነቱ ሰማይ ነካ:: ታዲያ ምን ዋጋ አለው! ናርዶስ በግድ ታፍሶ ዘመተ:: አሁን ላይ ይሙት ይዳን መገመት አይቻልም:: ገሚሶቹ ከጎንድ መንግሥቱ ጋር ሐረሬ ገብቷል ቢሉም መርዶ ነጋሪዎች ይበዛሉ:: በዘመቻው ወቅት እኔ በጭንቅ ተረፍሁ:: እሱ ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ታፍሶ በመጋጃ መሳይ መኪና ተጫነ:: እኛ ልንጫን ከጎጇችን ወጥተን እንደ ተከበብን መኪናው ሞላ::





ለሁለተኛ ዙር መኪናውን መጠበቅ ጀመርን:: ያ መጋጃ መኪና እነ ናርዶስን ጦር ግንባር አድርሶ ቀሪዎችን ሊጭን ተመልሶ ከተፍ አለ:: ወፌ ሰማይ ተማሪዎች ወደ መኪናው ሲጫኑ የቅኔ መምህራችን ደረሱ:: ከመኪናው እንደወጣን ውረዱ ሲሉ ትእዛዝ ሰጡ::

ወታደሩ አንድ ተማሪ ከመኪናው ከወረደ በጥይት ሰብሬ እጥለዋለሁ ካለ በኋላ ሾፌሩ እንዲቀጠል ትእዛዝ ሰጠ:: እኔም ከመኪናው ላይ ወጥቼ ነበር::" ሲል በመኻል ተፈሪን ድጋሜ የእንባ ማዕበል ተናነቃቸው:: አሁንም ቦሩ ሜዳ ላይ የመጨረሻውን ልቅሶ አለቀሱ::

ወጣቱ ሊቅ ግን ቀጠለ::

"እንዳልኋችሁ ለዘመቻ ከታፈሱት የአብነት ተማሪዎች መኻል በእድሜ ትልቁ እኔ ነበርሁ:: መኪናው ላይ ተጭነን መምህራችን ውረዱ፣ ወታደሩ ቀጥሉ ሲል ሾፌሩ መኪናውን መዘወር ጀመረ:: መኪናው ግን የየኔታን ትእዛዝ ሊጥስ አልቻለም:: እንደተገተረ ቀረ:: የኔታ ናቸው እንዳይንቀሳቀስ በድግምት ቀጥ ያደረጉት:: ወደ ኋላ ሲነዳው ይሽከረከራል:: ወደፊት ሲለው ወደ ግራ ዘመም ብሎ ቀጥ ይላል:: በመጨረሻ ወታደሩ ወደ መኪናው ወጥቶ በንዴት እያነሣ ወደ መሬት ፈጠረቀን:: ጠጠር ላይ ወደቅን:: አንዲት ጠጠር

ተፈናጥራ ፊት ጥርሴን ገጨቻት፡፡ ፊት ጥርሴ የተሸረፈችው ያን ቀን ነው፡፡ ከመኪናው ተገፍትሬ የወደቅሁ ቀን፡፡" ሲል መርዶኛው ወደ ጥርሱ ቀና አለ፡፡ ፊት ጥርሱ ሸራፋ ናት፡፡ በጥቂቱም አምሳለች፡፡

ገበዚህ መንፈስ ከዘመቻ ከተረፍን በኋላ ትኔ ቤቴ ተፈታ፡፡ እኔ ወደቦሩ ሜዳ መጥቼ መለሎ የመሰለች ሚስት አገባሁ፡፡" ካለ በኋላ ሚስቱን በፍቅር ዐይን ተመልክቶ

"ከትኔ ቤት የተመለስሁ ቀን ውኃ ስትቀዳ ከወንዙ ዳር ደረስሁባት፡፡ ገና ከእናቴ ቤት አልደረስሁም ነበር፡፡ እሷን ሳያት "ናርዶስ" ትዝ አለኝ፡፡ ናርዶስን የመሰለ ልጅ መውለድ እንዳለብኝ ውስጤ አመነ፡፡ በመንፈቅ ተጋባን፡፡ ሌሊት ሌሊት የናርዶስን ውበት አተርክላት ጀመር፡፡ ባመቱ ናርዶስን የመሰለ ልጅ ወለደች፡፡ የበኵር ልጄ የናርዶስን ውበት ይዞ ተወለደ፡፡ ናርዶስ ባጠገቤ ቢኖር ኑሮ በሚስቴ ሳልጠረጥረው አልቀርም ነበር፡፡ እኔ ልጄን ከቀለሙ ጋር እንዳይኮበልል ዐሥራ ይገኔ አስቀረሁት፡፡" ብሎ ቁጭ አለ፡፡

ተፈሪ ዘቦሩ ሜዳ ግን ቀጠሉ፡፡

"ቀለሙ ሲወለድ የቀለም ቀንዱን የአካልዬን ታሪክ እየተረከሁ አሳደግሁት፡፡ የገብርዬን ጭምር፡፡





"ይማራል እንደ አካልዬ፡፡

ይዋጋል እንደ ገብርዬ፡፡"

ብዬ ሳልፈጽም ስለ አካልዬ በልጅነት እንደበቱ እየተኮላተፈ ይጠይቀኛል፡፡ ከናፈሩን ስሜ 'አካልዬ የቀለም ቀንድ ናቸው፡፡ የቅኔ ትምህርታቸው ከቅኔ ከመጽሐፍ ከአቡሻህር ይቀዳል፡፡ የቅኔ ሊቅነታቸው ከጎጃም፣ የመጽሐፍ ሊቅነታቸው ከሸዋ አንኮበር፣ የአቡሻህር ቀመራቸው ከጎንደር ሣሕለ ወልድ ይመዘዛል' እያልሁ አሳደግሁት፡፡ ትምህርት ሲጀምር ግን ዝምተኛ ኾነ፡፡ አርምሞ የተመሰጠ ምንጭ ስለሆነ የቀለም ሰው መሆኑን ገመትሁ፡፡ ባመቱ ጓደኞቹ ነበልባል የሚል ስም አወጡለት፡፡ ከሰው ምላስ ይገባል ብዬ ቀለሙ አልሁት፡፡" ታሪኩን ሲተርኩ እንባቸው ወርዶ ወርዶ ጢማቸውን አራሰው፡፡ ባለቤታቸው በልቅሶ ብዛት ጉሮሯዋ ደርቋል፡፡ ከእንባ በቀር ቃል አይወጣትም፡፡ ሰውነቷም መንምኗል፡፡

"ይኸው ልጄ ቀለሜ! ቀለሜ ልጄ! ኪነ ጥበብ የሚባል የዋሽራ ተማሪ ተከትሎ ጎጃም ገባ፡፡ ከጎጃም በኋላ የደረሰበት አልታወቀም፡፡ የጎጃምን ተማሪዎች ስጠይቅ 'ከሞተም ሞተ ነው፡፡ ካልሞተ ደግሞ እንደ ተዋነይ ተሰውሮ በሕይወት ይኖር ይሆናል' እያሉ ተዘባበቱብኝ፡፡ ደንቢያ ወርጄ ጎንደር ወጥቼ ትግራይን አዳርሼ የውኃ ሽታ ሲሆንብኝ እያለቀስሁ

ወደ ሀገሬ ተመለስሁ። በውስጤ መርዶውን ከተረዳሁ ቆይቻለሁ። ይሙት ይዳን እርግጠኛ ባልሆነው ልጁ ዛሬ የአደባባይ መርዶ ጠራሁ። ትዝታው ሥቃይ ቢሆንብኝ እንደምንም እችለዋለሁ። ቀኔ ቢጨልምም እችለዋለሁ።" ብለው መርዶውን ካረዱ በኋላ ሕዝቡ በትኩስ እንባ ተሰናበታቸው። ዐራት ዐይናው ተፈሪ በሳምንቱ አሸለቡ። ከቀለም ቀንዱ አካለ-ወልድ ለጥቆ በሩ ሜዳ ሁለተኛውን ሊቅ አጣች። በመንፈቅ ሚስታቸው ተከተለች።





# ፫

ጎንጅ- ጎጃም

ሐሽማል ከመሆናቸው በፊት የተዋነይን ውኃ መጠጣት ነበረባቸው። ሁለቱ ተማሪዎች ከውኃዋ ከተጎነጩ በኋላ ሊቁ ፋሪስ አንድ ታሪክ መዘዙ።

"እኔና ቀለሙ ተፈሪ ይችን ውኃ የጠጣን ቀን ደስታው ሊያሳብደን ደርሶ ነበር። ቀለሙ ከወሎ ሲመጣ ገና ብላቴና ነበር። ኪነ ጥበብ ከሚባል ብስል ተማሪ ጋር መጥቶ የተዋነይን የቅኔ መንገድ ቀጸለ። ከዚያ በፊት የዋድላውን የቅኔ መንገድ በደንብ ያውቀዋል። የኢትዮጵያ ዐውደ ዓመት መባቻ ቅዳሜ ቀን በባተበት የዓመቱ መጨረሻ ቅዳሜ ቀን ከውኃዋ አብረን ጠጣን። ክስተቷ በዚያ ቀን ነበር። ከዚያ በፊት ያችን የምሥጢር ቀን ስንጠብቅ ዓመታትን አሳልፈናል። ደጅ ጥናታችን የወግ አልነበረም። ሕይወትን ፍለጋ እንደ እኛ የተንከራተተ በሀገር የለም። ከርታታ ኮከቦች ነበርን። ለዓመታት ተክዘናል። ውኃዋን ከጠጣን በኋላ ሐሽማል የመሆን መንፈስ ተጠናወተን።" ሲሉ ገሞራው

"የእኔም ምርጫ ተመሳሳይ ነው፡፡ ከተዋነይ ዓለም ገብቼ በስዋሩ መኖር እፈልጋለሁ፡፡ ስለ ተዋነይ ስሰማው ያደግሁት አፈ-ታሪክ መስጦኛል፡፡ በተለይ መልአከ-ሞትን የገዘተበት ምሥጢር ከአእምሮ በላይ ነው፡፡ እንደ ተዋነይ ከመልአከ ሞት ተሰውሬ መኖርን እመርጣለሁ፡፡" ሲል ጨመረበት፡፡

"ለመሆኑ የተዋነይ ዓለም ስትሉ ምን እያላችሁ ነው? ለተዋነይ ምን የተለየ ዓለም አለው?" አሉ ምንም ያልገባቸው መስለው፡፡

ታሪኩ ፈጠን ብሎ ማብራራት ቀጠለ፡፡

"በቅኔ ቤት አፈ-ታሪክ ስለ ተዋነይ ብዙ ብዙ ይወራል፡፡ እውነታው ግን ተገልጦ አልታወቀም፡፡ ከእኒህ ወሬዎች መካከል የእሱ ዓለም የሚባለው ደግሞ ስዉሩ ዓለም ነው፡፡ የድሮ ሊቆች ከተዋነይ አብነት ይዘው ከመኻል ሀገር በየቅኔ ቤቱ እየኮበለሉ የሚሰወሩት ስዉር ዓለም አለ ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ እኒህ የቅኔ ሊቆች ከተዋነይ ዓለም ሲገቡ መልአከ ሞትን የሚገዝቱበት ጥበብም ምሥጢርም ሆኖ በዚሁ ስዉር ዓለም እንዳለ ይወራል፡፡ መልአከ ሞትን ለመገዘት ያንን ዓለም መቀላቀል እፈልጋለሁ፡፡ ደግሞ...፡፡" ታሪኩ ከውስጡ የተቀጣጠለውን ሐሳብ ከከንፈሩ አድርሶ ሲመልሰው





"በደንብ አምጣው እንጂ፡፡ ከጀመርኸው በደንብ አፍታታው፡፡" ሲሉ አበረታቱት -ሊቁ፡፡

"ልጅ እያለሁ የሰማሁት ወሬ ነው፡፡ ድሮ ወደ ስዉሩ ዓለም ብዙ ብዙ የቆሎ ተማሪዎች ይሄዱ ነበር አሉ፡፡ ከሄዱ በኋላ ተሰውረው የሚቀሩ ሲኖሩ ከፊሎቹ ግን ተመልሰው ይመጣሉ ይባላል፡፡ እንዲያውም በቅርብ የሰማሁት ወሬ አለ፡፡

ከዋሸራ ቅኔ ቤት ሁለት ተማሪዎች ወደ ተዋነይ ዓለም ሂደው ነበር፡፡ አንዱ ተሰውሮ ሲቀር ኋደኛው ተመልሶ መጣ፡፡ ተሰውሮ የቀረው ወንድሞች ግን ስዋሬውን ሲያምኑ አልቻሉም፡፡ ወንድማችንን የአውሬ ሲሳይ አድርገኸው ተመለስህ ብለው ተጣሉት፡፡ ጎጃምን ለቅቆ ወደጎንደር መጣ፡፡ አሁንም ጎንደር መጽሐፍ እየተማረ ይገኛል፡፡ ተሰውሮ የቀረው ግን የመልአከ ሞትን መግቻ እንደ ጨበጠ በከፊል አጫውቶኛል፡፡ ይቺ ውኃ ወደ ስዉሩ ዓለም የምትመራ ከሆነ ስዉሩን ዓለም መርጫለሁ፡፡ ወደዚያው ይላኩኝ፡፡" ታሪኩ እጅ ነሥቶ በተማሪ ወግ ተማጠናቸው፡፡

ሊቁ በመገረም

"አወይ! አወይ! ተማሪ የሰማው ምሥጢር! አወይ! አወይ!፡፡" ካሉ በኋላ ጥቂት ማብራሪያ ቢጤ አከሉበት፡፡

"ከስዉሩ ዓለም በፊት የሞት መንገድ ቅርብ ነው:: እኔ ልጅ እያለሁ ለፍቸበታለሁ:: ስዉሩ ዓለም የወንዶችና የሴቶች ዓለም ነው::

በዚያ ስፍራ ወንዶች ቢስ ልበ-ቢስ ናቸው:: አእምሯቸው ብዙ አያሰላስልም:: ሴቶች ግን አሳቶች ናቸው:: ከመኻል ሀገር ወደ ስዉሩ ዓለም ለሄደ ወንድ ለፍቅር ቅርብ ልብ አላቸው:: ፍቅር ይወዳሉ:: አብረዋቸው ከሚኖሩ ልበ ቢስ ወንዶች ጋር የሚኖሩት የተፈጥሮ ምሥጢር ኾኖባቸው እንጂ ከልበ ቢሶች ጋር በትዳር ቢኖሩም በመካከላቸው ክፍተት አለ:: ሴቶች በወንዶች አይኮሩም:: ስለዚህ ከመኻል ሀገር ወንዶች ሲሄዱ ሴቶች ደስታውን አይችሉትም:: ወንዶች ግን ከመኻል ሀገር በሄዱ ወንዶች ላይ መራራ ጥላቻ አለባቸው:: ለሞት የምትጋለጡት ከዚህ ላይ ነው::" አሉ ሲቁ ፋራስ ዘጎንጅ::

"እንዴት?" አለ ገሞራው ግራ ገብቶት::

"ከራሴ ታሪክ ተነሥቼ ላውጋህ:: ልጅ ሁኜ የቅኔ ዘራፊ እያለሁ እኔ፣ ቀለሙና ኪነ ጥበብ ወደስዉሩ ዓለም ልንቀላቀል ሄድን:: አካሄዳችን የሞት መግቻ ጥበብ ነሠሣ ነበር:: ይህ የመልእክ ሞት መግቻ ደግሞ በሴቶች መዳፍ ብቻ እንዳለ ሰምተናል:: በተለይ ተዋነይ ሞትን ለመገዘት





ከስዉሩ ዓለም ውስጥ ከሴት እጅ እንደተቀበለው ዘወትር የሚተረክ ታሪክ ነው:: ከዚህ ተነሥቶ ከዛር . ጋር ጋብቻ ፈጽሞ ነበር እስከ መባል ደርሷል::

እኛም በተዋነይ መንገድ ገስግሰን ስዉሩ ዓለም ወደሚገኝበት ወደ ደቅ እስጢፋ ወረድን:: ደቅ ስንደርስ ምንም አላገኘም:: ለዐራት ዓመት ያኽል ከአንዲት ወንዝ ሥር ተኮልኩለን ኖርን:: ከዐራት ዓመታት በኋላ ሁለት ሴቶች ውኃ ሊቀዱ መጡ:: እኛ ከውኃዋ ዳር ተኝተን ነበር:: ቀለሙና ኪነ ጥበብን እንቅልፍ ጥሏቸዋል:: እኔ ቁጭ ብዬ አስባለሁ:: አንዷ ሴት መጥታ የኪነ ጥበብን ክንድ ጨበጠችው:: ነቅነቅ አላለም:: ሁለተኛዋ ደግሞ በደስታ ተውጣ የቀለሙ ተፈሪን ግራ ጣት ጨብጣ "እስመ ንድፍት አነ በፍቅሩ:: የማኑ ተንቅፈኒ ወጸጋሙ ታሕተ ርእስየ፤ በፍቅሩ ተነድፌአለሁና ቀኙ ታቅፈኛለች ግራው ከራሴ በታች ናት" እያለች ለፈለፈች:: ቀለሙ እንደ ተኛ ነበር:: እንቅልፍ "ጅው..ጅው..ጅ..ው" አድርጎ ወስዶታል:: እኔ ግራ በመጋባት ውስጥ ሆኜ ቁልጭ ቁልጭ እያልሁ እመለከታለሁ:: ቀለሙና ኪነ ጥበብ ደንዝዘዋል መሰል ነቅነቅ አላሉም:: ጥቂት ቆይቶ ቀለሙ ተፈሪ ቁልጭ ቁልጭ ሲል ዐየሁት:: ከዚያ ኪነ ጥበብ እንደ መበርገግ ብሎ ሲነሣ ቄጠማ የመሰለች መልከ-መልካም ሴት ከአጠገቡ ቆሟለች:: ኪነ ከድንጋጤው የተነሣ ሰማይ



Scanned with CamScanner

እንዲሁ ፈቀደችለት። ባይገርምህ ራሷ መኻል ሀገር አድርሳው ተመለሰች። ዕፁ ዕፀ-መሰዉር መሆኑንም የተረዳሁት ለዚህ ነው።" አሉ ሲቁ እየሳቁ

"እሺ በማርያም እንዴት አድርጋ ነው እንደተሰወረ በደመና ጭና አመጣችው ወይስ በእግራቸው?" አለ ታሪኩ። "በስዋሬ እንዳመጣችው ኪነጥ በብ በአንደበቱ አጫውቶኛል። በደመና መሆኑን ግን ሳረጋግጥ አልቻልሁም።" ሲሉ አከሉት።

"እንዴት መሰላችሁ ልጆቼ? ኪነ ጥበብ ተሰናብቶ ወደ ሀገሩ ለመመለስ ሲነሣ ተከተለችው። በሳምንቱ እያዘገሙ ተያይዘው ዋሸራ ገቡ። ከስዉሩ ዓለም እስከ ዋሸራ ሲመጡ ግን ኪነ የተሰወረ አልመሰለውም ነበር። እያወጉ ዋሸራ ሲደርሱ በአጋጣሚ በዋሸራ ማርያም ትልቅ ሊቅ አርፈው ልቅሶ ነበር። ኪነ ጥበብ ከልቅሶው ደርሶ ወደ ካህናቱ ሲጠጋ ሴቷ ጣቱን ፈጥርቃ ያዘችዉ። ከዚያም ያችን የተፈጥሮ ቀለበት ከጣቱ ላጥ ስታደርግበት ከዋሸራ ማርያም ካህናት መካከል ተገለጠ። ዘወር ሲል እሷ ከአጠገቡ የለችም። ጥቂት ፈዝዞ ከቆየ በኋላ ዋሸራ መድረሱን የተረዳው ማዕበል ፈንቴ መወድስ ሲዘርፉ አይቶ ነው። ከስዉሩ ዓለም እስከ ዋሸራ ማርያም ተሰውሮ የመጣ አልመሰለውም ነበር። እንግዲህ በስዉሩ ዓለም ውስጥ የሚፈለጉት ወንዶች ሳይሆኑ ሴቶች





ናቸው ያልሁት ለዚህ ነው። የሞቱ መግቻም ያለው በሴቶች መዳፍ ብቻ ነው። ከዚህ ላይ ልብ ማለት ይገባል።" ማብራሪያውን ገታ አድርገው ሁለቱን ተመለከቷቸው። አፋቸውን ከፍተው እየተመሰጡ ነበር።

"ከዚህ ላይ ልብ ማለት ይገባል። የሀገሬ ሰው ተዋነይ በአስማት ከዛር ጋር ተጋብቶ ልጅ ወልዷል የሚለውን ቁንጽል ታሪክ ይዞ ሳያጠራ ነው። ምን መሰላችሁ? ቀስሙና ኪነም ሆነ እኔው ራሴ በተዋነይ መንገድ ለመሄድ ሞክረን ነበር። ኪነ ጥበብ ይችን ሴት አግብቶ በፍቅር ኑሯል። እንደነገርኳችሁ የፍቅሩ ምንጭ ግን የመጣው ከስዉሩ ዓለም ሴቶች ነው። ከኪነጥበብ አይደለም። ነገር ግን ኪነ ጥበብን ሴቷ ለፍቅር እንደፈለገችው በጊዜው ተዋነይን ከስዉሩ ዓለም አንዷ ለፍቅር ፈልጋው ነበር። ተዋነይም ሴቷ ጋር ተቀራርቦ ነበር። ከሴቷ እጅ የሞት መግቻውን ጥበብ ተምሮ ሰባት ዓመት መልአከ ሞትን እንደገዘተው እናውቃለን።

ከሴቷ ጋር ጋብቻ መፈጸሙን ግን አስረግጦ ያወጋን የለም። የጎንጅ ሊቆች የምናውቀው ከስዉሩ ዓለም ከአንድ እስከ ሰባተኛው ጥበብ ድረስ ቀስሞ መመለሱን ነው። በእርግጥ ከተዋነይ ይልቅ ኪነ ጥበብ እድለኛ ነበር። ተዋነይ ከስዉሩ ዓለም ወደመኻል ሀገር ሊመለስ ሲፈልግ ጥበብ



Scanned with CamScanner

ያስተማረችው ቆንጆ ሴት ተጣልታው ነበር፡፡ ከጠቡ መካረር የተነሣ "ምልዋጥ" ድረስ ተጠቅማለች፡፡ ማለቱ ተዋነይ ውሻ መስሎ ከስዉሩ ዓለም ሲወጣ ሲል አራስ ነብር መስላ ከራሱ ላይ ቂብ ብላ አስደንብራዋለች፡፡ ዶሮ' መስሎ ሲያመልጣት ሲል ጭልፊት ሆና አንቃዋለች፡፡ በመጨረሻ ትኋን ሆኖ በሚራራ ነጋዴዎች አትማዳ ላይ ለክክ ብሎ ከስዉሩ ዓለም ወደ ጎንጅ ተመለሰ፡፡ ስሙም ተኋናይ ተባለ፡፡ ተዋነይ እየቆየ የተሸሻለ ስሙ ነው፡፡" ሊቁ ዛሬ ም/''ጢር አልተረፋቸውም፡፡ ገሞራው ሲያዳምጥ ቆይቶ "አታጋልጠኝ ነው ማለት" ካለ በኋላ

"ለመሆኑ ኪነ ጥበብ ከስዉሩ ዓለም ከሴቷ ቤት ሲደርስ ምን ገጥሞት ይሆን?" አለ፡፡

"ቤቷ እንደገባ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ባሏ ከአውሬ አደን ተመለሰ፡፡

ጦሩን ገትሮ ሲመጣ ኪነጥበብን በመጋረጃ ከለለችው፡፡ ባሏ ግን ሌላ ወንድ ወደ ቤቱ እንደገባ ጠርጥሯል፡፡ ወደቤት እንደገባ "አዳም አዳም" ሸተተኝ ሲል አፈጠጠባት፡፡ በእነሱ ዘይቤ ከመኻል ሀገር የምንሄደው ወንዶች አዳም ነው የሚሉን፡፡ ባሏ 'እኔ ከወጣሁ በኋላ ወደ ቤቴ "ሌላ አዲስ አዳም" ገብቷል፡፡ ያንን አዳም በዚህ ጦር እዘክዝከዋለሁ' ብሎ





ጓዳ ጎድጓዳውን ይፈትሽ ጀመር፡፡ ነገር ግን በባሕላቸው አንድ ትልቅ ምሥጢር አለ፡፡ ባሏ ጦሩን ይዞ ሲንጎራደድ ውኃ በገበታ አቅርባ ጦሩን ከገበታው ውኃ ዘፈዘፈችው፡፡ ጦሩ ሲቀዘቅዝ የሰውዬው ንዴት አብሮ በረደ፡፡ ቀጥሎ ገንፎ አቀረበችለት፡፡ ያንን ከተመገበ በኋላ ንዴቱ በረደ፡፡ በስዉሩ ዓለም ያሉ ወንዶች ልበቢስ ናቸው ያልሁት ከዚህ ላይ ነው፡፡ ይህ ባሕላቸው ነው፡፡ ንዴቱ ከበረደ በኋላ ኪነ ጥበብን ከተሰወረበት አምጥታ ከባሏ ጋር አስተዋወቀችው፡፡ እንደ ነገርሁህ ወንዶች ልበ-ቢስ ስለሆኑ ወዲያው ይረሳሉ፡፡ እሱም ቂሙን ረስቶ እንደ ጓደኛው ቆጠረው፡፡ መጀመሪያ እንደ መጣ አግኝቶት ቢሆን ኑሮ በሕይወት አይመለስም ነበር፡፡ በሴቷ ፍቅር ተፈወሰ፡፡ ፈላስፎች "ሴት ፍቅር ናት" የሚሉት ከዚህ ተነሥተው ነው፡፡" ብለው ዝም ሲሉ

"ይህስ ይሁን፡፡ ኪነ ጥበብ ከሴቷ ምን ቁም ነገር አገኘ? እንደ ተዋነይ መልአከ ሞትን መገዘት ቻለ?" አለ ገሞራው፡፡

"ከጥበብ ሌላ ምን ቁም ነገር ይወርሳል፡፡ ጥበብ ነዋ! ያው ከመኻል ሀገር እንደሚሄዱ ተማሪዎች ጥበብ ወረሰ፡፡ ከሞት መግቻው ጀምሮ ያሉ ውድ ውድ ጥበባት በሴቶች እጅ ናቸው፡፡ እሱን ወረሰ፡፡ በስዉሩ ዓለም ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች ድርሻ አላቸው ያሉት ከዚህ ላይ ነው፡፡ በዚህ ስዉር

ዓለም የበላይ ሴቶች ናቸው። በመኻል ሀገር ከሴቶች ይልቅ በከፊል የወንዶች የበላይነት ይንጸባረቃል። በስዉሩ ዓለም ደግሞ ከወንዶች ይልቅ የሴቶች የበላይነት ይጉላል።" እሱ ፋሬስ ስለ ስዉሩ ዓለም እየተነተነ።

"እሺ የኔታዬ ሁኔታው ግሩም ነው። ኪን ጥበብ ሲመለስ ቀለሙ ተፈሪ ከስዉሩ ዓለም እንደገባ ቀረ ወይስ ተመለሰ?"

"ቀለሙ ድሮ እንደ እኔ የጎንጅ የቅኔ ተማሪ ነበር። ከተዋነይ ጥበብ ሲቋደስ ደቅ ከገባ በኋላ ቀንቶት ወደስዉሩ ዓለም ገብቶ ከሴቶች መዳፍ የሞት መግቻውን ጥበበ ተዋነይ ከጨበጠ በኋላ መኻል ሀገር የሚሄዱ ጥበብ ፈላጊዎችን የሚያስተናግደው እሱ ነው። በማዕረግ ስሙ ዐራት ዐይናው ቀለሙ ተፈሪ ይባላል። አቡሻህሩን ጭምር በልቶታል። የስዉሩን ዓለም ታሪክም ቁልጭ አድርጎ ቀጽሎታል። እንደ ወረደ የቀጸለው ከሴቶች ነው። ከእሱ በፊትም ሆነ በኋላ ወደስዉሩ ዓለም ከገቡ ጠቢባን ጋር እየተመካከረ ከመኻል ሀገር ጥበብ ፈልገው የሚሄዱ የቅኔ ተማሪዎችን ወደውስጥ ያስገባል። ከመኻል ሀገር ወደስዉሩ ዓለም የሚሄዱ ሰዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል። ከጠቢባኑ አስፈቅዶ ወደ ሴቶች ስዉር ዓለም ይልካል፥ እኒህ ጠቢባንም እንደ እሱ ጥበብ ፍለጋ ሂደው በስዉሩ ዓለም ውስጥ ለብቻቸው የሚኖሩ ናቸው።





ከሴቶች መዳፍ እንደ ተዋነይ የሞት መግቻውን ከወረሱ በኋላ ወደመኻል ሀገር አልተመለሱም። አሁንም በስዉሩ ዓለም እየኖሩ ከመኻል ሀገር የሚመጣው ሁሉ ወደ ሴቶች ስዉር ዓለም እንዳይገባ ዘብ ቁመዋል እሱ። እናንተም ከስዉሩ ዓለም ገብታችሁ ከሴቶች መዳፍ የመልአከ ሞትን መግቻ ለማግኘት ከቀለሙ ተፈሪ ጀምሮ በዚያ የሚኖሩ የጠቢባኑን ፈቃድ መያዝ ግድ ይልባችኋል። ለማንኛውም እኔ ለዐራት ዐይናው ሲቅ ቀለሙ ተፈሪ ደብዳቤ ጽፌ እልካችኋለሁ። ከሴቶች መዳፍ የሞት መግቻውን እንድታገኙ እሱ ይረዳችኋል። ቀለሙ ከ"ከርታታ ኮከቦች" አንዱ ሁኗል።" ካሉ በኋላ ሸብረክ ብለው በተባ ብዕራቸው ደብዳቤውን ይሞነጫጭሩ ጀመር።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)



Scanned with CamScanner

## ፬

### ደቅ እስጢፋ

በሀገራችን ደቅ ደቅ ደቅ በሚል ስም የሚታወቁ ሦስት መካናት አሉ፡፡

እነሀም

ደቅ ደሴት- ጣና ውስጥ

ደቅ ጫራ-- ዳንግላ ግርጌ

ደቅ እስጢፋ-ስዉሩ ዓለም ናቸው፡፡ ጣናን ለጎበኘ "ደቅ ደሴት" ሲነሣ አዲስ ስም ሊሆንበት አይችልም፡፡ ለዳንግላ ልጆች ደግሞ "ደቅ ጫራ" ቅርባቸው ነው፡፡ እንደ እኔ የቅኔ ተማሪ ለሆነ ደግሞ የተዋነይን የጥበብ ዓለም ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ደቅ እስጢፋ ይባላል፡፡ ደቅ እስጢፋ የጠቢባንና የቅዱሳን ከተማ እንደሆነ ቢታወቅም ከጠቢባኑ ጎን ለጎን በስዋሬ የሚኖሩ በጥበብ አንቱ የተባሉ ሴቶች እንዳሉ ይታመናል፡፡ የቅኔ ሊቆች ተዋነይ የንጉሡን ሚስት ፍቅር ያስተማረበት የፍቅር ከተማ ማለት በሀገራችን ጫፍ ያለው ትክክለኛው "ደቅ እስጢፋ" ነው ሲሉ ከቅኔ ቤታቸው ቁጭ ብለው





አካባቢውን በዘንግ ጠቅሰው ያሳያሉ፡፡ የእኔ ቢጤ ፈሪዎች ደግሞ ሞትን ለመገዘት ይመላለሱበታል፡፡

ከፊል ተመራማሪዎች ተዋነይ በጢስ ተጠቅልሎ በደመና ተጭኖ ይመላለስ እንደ ነበር ይተርካሉ፡፡ እኔን ጨምሮ ከፊል የቅኔ ተማሪዎች ተዋነይን ለመሆን ውልብ ብሎብን ደቅ እስጢፋ ተቀላቅለን መልአከ ሞትን ለመገዘት ዳክረናል፡፡ አሁንም ጎሠሣ ላይ ነን፡፡

ቀለሙ ዘቦሩ ሥላሴ ግን ስዉሩን ዓለም ከተቀላቀሉ አያሌ ዓመታትን አስቆጠሩ፡፡ ዳሩ ግን በጠቢባኑ ዘንድ ረጅም ዓመት ዘልዛላ እድሜ የለም፡፡ እድሜ ማለት እንደ ተዋነይ ሞትን በመገዘት ከምእት ዓመት በላይ መኖር ነውና! ቀለሙ ከምንኩስና በቀር ሁሉን ፈተና አልፈዋል፡፡ ተራ መናኒ መስለው ከገዳም እስከ ደብር፣ ከደብር እስከገጠር ማንኛውንም የአብነት ቀለም ቀስመዋል፡፡ አሁን ግን ራሳቸው እንደ ተዋነይ ስማቸው የሚጠቀስ አብነት ሁነዋል፡፡

እነሆ በስዉሩ ዓለም ውስጥ ከዘግባው በስተጀርባ የሚኖሩ ከርታታ ኮከቦች ለትልቅ ምሥጢር ተሰብስበዋል፡፡ በስዉሩ ዓለም ያሉ ጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ ናቸው፡፡ ጉባኤው ሲጀመር ከቅኔ ቤት ተነሥተው ወደ ስዉሩ ዓለም ከፈለሱት አያሌ



Scanned with CamScanner

ሲ.ታውንት መካከል ዐራት ዐይናው ቀለሙና ጠቢቡ ሓረ ተሰየሙ:: ከገዳማውያን በኩል ወይራው ተገኙ::

ከዓለምም፣ ከገዳምም ዘወር ዘወር ብለው እውቀት የቀሰሙ ደግሞ ደቀኛው ታደሙ:: ጉባኤው ሲጀመር የጉባኤው መሪ ዐራት ዐይናው ቀለሙ ዘቦሩ ሥላሴ ነበሩ:: ውይይቱን እንዲህ ሲሉ ከፈቱት!!

"ከቦሩ ሥላሴ እስከ ደብረ ቢዘን ተንከራራትቼ ተንከራትቼ የአብነት ቀለማትን ቀስሜ በመጨረሻ ወደ ስዉሩ ዓለም ስመጣ ይህ ዓለም ምሥጢሩ የተጠበቀ እንደ ስሙ ስዉር ዓለም ነበር:: ከቅኔ ተማሪዎች በቀር ማንም የማይደርስበት ስዉር ዓለም ሳገኝ አባቴንና እናቴን ረሳኋቸው:: የመጨረሻ ልጃቸው እኔ ነበርሁ:: ለእናቴ የተለየ ተሰጥዎ አላት:: የአምባሰልን ዜማ ስታንጎራጉር ልብ ትበላለች:: እድል ቀብራት ቀረች እንጂ እንደ ወሎዬነቷ ዜመኛ ነበረች:: በተለይ አባቴ የሚረሳ ሰው አልነበረም:: እንደ አካልዬ ዘቦሩ ሜዳ ዐራት ዐይና ሊቅ ነበር:: አቡሻህሩን የቀጸለው ከአቡነ ጴጥሮስ ጋር ነው:: ከአቡነ ጴጥሮስ ጋር ከአካልዬ መጽሐፍ ቤት አብረው ነበሩ:: አቡነ ጴጥሮስ ሰማዕት ሲሆኑ አባቴ ሚስት አገባ:: ከዚያ እኔ ተወለድሁ:: አባቴ እግር ሥር ቁጭ ብዬ ቀለም እያጠናሁ አደግሁ:: እግረ መንገዱን አባቴ ታሪክ





እያስጠና አሳደገኝ:: የታላላቆችን ታሪክ ነው ያስተማረኝ:: ጽፎ ያላሳተምሁት ምርጥ ምርጥ የሊቆች የሕይወት ጦማር ከእጄ ላይ ይገኛል:: ወደዚህ ዓለም ባልመጣ ኑሮ ደራሲ እሆን ነበር::

በእርግጥ አሁንም ራሴን ከደራሲ እኩል እቆጥረዋለሁ:: የጻፍሁት ባይታተምም ከእጄ ላይ የሊቆች ምዕላድ አለ:: አባቴ ሲናፍቀኝ ያንን አነባለሁ:: አባቴ ካጠገቤ ቁጭ ብሎ የሚያወጋኝ ይመስለኛል:: እንደምታውቁት ወደ ስዉሩ ዓለም የመጣሁበት ዘመኑ ብዙ ነው:: ይህንን ያኽል ዘመን የኖርሁበትን ምሥጢር ሁላችሁም ታውቃላችሁ:: ዛሬ መናገር የፈለግሁት ግን ስለ አባቴ አይደለም:: ነገሬ ሌላ ነው::" ብለው ከርታታ ኮከቦችን በሰያፍ ተመለከቷቸው:: የዐራት ዐይናውን ብስል ሐሳብ ለመስማት ቋምጠዋል::

"ከዛሬ ጀምሮ ወደ ስዉሩ ዓለም የሚቀላቀሉ ሰዎች መታገድ አለባቸው:: እንዳይገቡ ይከልከሉ:: ቅኔ ቤቷን ያረገጠ እስኳላ ተማሪ ሁሉ እየመጣ ስዉሩን ዓለም እየሰለለ ስለሆነ በራችንን እንዝጋ:: ስዉሩ ዓለም ይከርቸም:: ድሮ ከመኻል ሀገር ሊቆች ሲመጡ ተቀብለን በፍቅር አስተናግደናቸዋል:: ከዛሬ ጀምሮ ግን ብናቆም የተሻለ ይመስለኛል:: የስዉሩ ዓለም ምሥጢር በመኻል ሀገር መወራት ስለጀመረ ወደ ስዉሩ

ዓለም የሚመጡ እየበረከቱ ነው፡፡ የእኔ ቢጤዎች ጭምር ከሞት ለማምለጥ ኀብስተ መናውን ለመስልቀጥ ስዉሩን ዓለም ጎሣጣ ጀምረዋል፡፡ እነሱን ተከትለው ነገ እነማን እንደሚመጡ አናውቅም፡፡ ሀገራችንን የሚበረትሱ ባዕዳን ስተት ብለው ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ወደዚህ ዓለም የሚመላለሱ ሰዎች እኛን መስለው መኖር ስለማይችሉ ከአሁኗ ሰዓት ጀምሮ ወደ ስዉሩ ዓለም መግባት የለባቸውም፡፡ ተስማምተን እንዘጋው፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው ቀለሙ በመጀመሪያው እለት ጉባኤውን በንግግር ሲከፍቱ፡፡

ከዐራት ዐይናው ቀለሙ ቀጥለው ከጉባኤው መካከል ቀድመው የተነሡት ከርታታው ኮከብ ደቀኛው ነበሩ፡፡ ደቀኛው ከስዉሩ ዓለም ተነሥተው ወደ መኻል ሀገር ብቅ እያሉ አንዳንድ ቁም ነገር እየከተቡ ወደ ስዉሩ ዓለም ይመለሳሉ፡፡ ዘለዓለም ከርታታ ናቸው፡፡ ከርታታ ኮከቦች የዚች ዓለም ጌጥ ቢሆኑም ቅሉ በሰማይ እንዳሉ ከርታታ ኮከቦች የተገለጠ ብርሃን የላቸውም፡፡ በስዋሬ ዘወር ዘወር ስለሚሉ ቁጥራቸው በሰማይ ካሉ ተከርታታ ኮከቦች እኩል ነው፡፡ እኒያ በሰማይ ያሉ ከርታታ ኮከቦች ለሌዳ እንጂ፣ ብርሃን እንደ ሌላቸው ይታወቃል፡፡ ደቀኛውም በመኻል ሀገር ሲንከራተቱ በስዉር እንጂ ተገልጠው እምብዛም ዘወር ዘወር ብለው አያውቁም፡፡ እንደ ከርታታ ኮከቦች በስዋሬ ነው፡፡





ከርታታ ኮከቦች ለሰማይ ጌጥ እንደሆኑ ደቀኛውም ለኢትዮጵያ የጥበብ ፈርጥ ናቸው፡፡ ስዋሬን እንደ ፈለጉ ይጠቀሙበታል፡፡ አሁን ላይ በስዋሬው በኩል የሚጠረጠሩትን የኤርትራውን መሪ ኢሳይያስ አፈወርቂን በእጥፍ ይበልጧቸዋል፡፡ እረ ከምን ተዳርሰው!

ለመናገር ሲነሡ ፈገግ ፈገግ አሉ፡፡

ከዚያም

"የተማረና የተመራመረ ቢኖር እርቆ ያስባል፡፡ ዐራት ዐይናው! ምነው እናትህ መንታ መንታውን ወልዳ ቢሆን? ሐሳቡን ሙሉ በሙሉ ተቀብየዋለሁ፡፡ ይህ ዓለም አሁን ድረስ ስዉር የሆነው ምሥጢሩ በሴቶች መዳፍ ስለሆነ ነው፡፡ ሴት በተፈጥሮዋ ምሥጢር ናት፡፡ ምሥጢሯን የምትፈታው ለወደደችው ብቻ ነው፡፡ በቀር ቁጥብ ናት፡፡ በአርምሞ ከምናውቃቸው ከአባ አጋቶን በላይ ምሥጢር አምቀው ይይዛሉ-ሴቶች፡፡ ያ ስለ ሆነ ስዉሩን ዓለም ጠብቀው አቆዩልን፡፡ እኛ ግን የሴቶችን ቃል እየጠበቅን አይደለም፡፡ አንዳንዶቻችን ከዚህ ተነሥተን ወደመኻል ሀገር መሄድ አብዝተናል፡፡ መሄዳችን ባልከፋ ነበር፡፡ በሄድን ቁጥር የስዉሩን ዓለም ምሥጢር ሹክ ስለምንል አዲሱ ትውልድ ወደዚህ ዓለም እየተመመ ነው፡፡ መንገድ ላይ የአውራ ሲሳይ

እየሆኑ የሚቀሩም አሉ፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ከመኻል ሀገር የሚመጡ የአብነትም ሆነ የአስኳላ ተማሪዎችን መቀበል የለብንም፡፡ እኛ እንበቃለን፡፡ በዚህ ስዉር ዓለም ያለን ጠቢባን ከበቂ በላይ ነን፡፡" አሉ ደቀኛው፡፡

ቀጥሎ ወይራው ተነሡ፡፡ በእድሜ የመጨረሻው አረጋዊ ናቸው፡፡ መኻል ሀገር ቢሆኑ ኑሮ ሙተው ተቀብረው ይረሱ ነበር፡፡ እንደተዋነይ ስዉሩን ዓለም ተቀላቅለው በመኖራቸው መልአከ ሞት ረስቷቸዋል፡፡ ከእድሜአቸው ብዛት የተነሣ ወይራው የሚል ቅጽል ስም አላቸው፡፡ ወገባቸው እንደወይራ ዛፍ ተጠማዝዞ ይኖራሉ፡፡ አጥንታቸው ደርቋል፡፡ የሚይዙትም ቆልማማ ከዘራ ሲሆን ከወይራ ዕፅ የተከዘረ ከዘራ ነው፡፡ ሲመለከቷቸው የነገር ሰው ይመስላሉ፡፡ ዳሩ ግን አይደሉም፡፡ ቆልማማውን ወይራ ከዘራቸውን ተደግፈው እንደተነሡ ቀጠሉ፡፡

"ያላችሁት ነገር ሁሉ ጥቂት ጥቂት እውነታ አለው፡፡ ነገር ግን ሴቶችን ማስፈቀድ አለብን፡፡ የዚህ ስዉር ዓለም ቤዛዎች ሴቶች ናቸው፡፡ እኛ የመጣነው ሴቶች ስላሉ ብቻ ነው፡፡ አሁን ድረስ ከሞት አፍ ያመለጥነው በሴቶች ጥበብ በኩል ነው፡፡ ሴቶች የመልአከ ሞትን መግቻ ባይሰጡን ኑሮ ሞት እንደጭልፊት ልፎ ይጨርሰን ነበር፡፡ ከመወሰናችን በፊት





ከሴቶች ጋር እንመካከር፡፡ እነሱ ከተስማሙ ወላ የቅኔ፣ ወላ አስኳላ ተማሪ ወላ የገዳም መናኒ ማንም ድርሽ እንዳይል እናደርጋለን፡፡

እንደምታውቁት ጃንሆይን ያኸል ሰው ከልክለናል፡፡ እኛ ተሰውረን ዝም ስንል ሞርካን ደጅ መጥናት ሺናሻ ለሺናሻ እንደ ተንጎራደዱ እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ሞርካ ዘሺናሻም ልቡን የሰጣቸው አይመስልም፡፡ ከጥበቡ ነፍጓቸዋል፡፡

እኛም የስዉሩን ዓለም ምሥጢር መጠበቅ አለብን፡፡ ወደመኻል ሀገር ሄደን ካላወራንና ወደዚህ የሚመጣውን ኮበሌ ካልተቀበልን የሚደፍረን የለም፡፡ ከሴቶች ጋር መክረን ዝም ጭጭ እንበል፡፡ እኛ በስዋሬ ከኖርን ደግሞ ማንም ሊያገኘን አይችልም፡፡" አሉ ወይራው፡፡

ወይራው ተናግረው ቁጭ ሲሉ ጠቢቡ ሖረ ተነሡ፡፡

"የመኻል ሀገር ሰዎች ወደዚህ የሚመጡት በዚህ ዓለም ውስጥ የከበሮና የዋሽንት ድምፅ እየሰሙ ነው፡፡ ከበሮ የምንደልቀው ዋሽንት የምናንቆረቁረው ደግሞ እኛው ነን፡፡ እነሱ ሲመጡ እኛ በስውር ከበሮ እየመታን ስንዘምር ይሰማሉ፡፡ ይህንን ምልክት ሲሰሙ ስፍራውን የሙጥኝ ይሉታል፡፡ ድምፁን ተስፋ አድርገው ደጅ ይጠናሉ፡፡ ልባችን



Scanned with CamScanner

ራርቶ የጠቢባኑን ዓለም እንዲቀሳቀሉ እንፈትዳለን:: እኛ በራችን ከዘጋን ዘጋን ነው:: ነገር ግን..." ጥልቅ ሐሳብ አናጠባቸው::

"እ..?እ..? ነገር ግን ወይራው እንዳሉት የስዉሩ ዓለም ቤዛዎች ሴቶች ናቸው:: ሴቶች መፍቀድ አለባቸው:: አብረው ያሉ ልበ ቢስ ወንዶችን በባሕላቸው መሠረት ያሳምኗቸዋል:: መጀመሪያ ሴቶች ፈቃደኛ ይሁኑ:: ሴቶች ካልፈቀዱ ማንም መጥቶ ቢቀሳቀል ዋጋ የለውም:: የሞት መግቻው ያለው በሴቶች መዳፍ ብቻ ስለሆነ ሴቶችን ይዘን ውሳኔውን እንወስን::" አሉ ጠቢቡ ሖረም::

ጠቢቡ ሖረ ተናግረው እንደ ፈጸሙ ዐራት ዐይናው ቀለሙ በረጅሙ ተነፈሱ:: ከዚያም

"አመሰግናለሁ አባቴ ወይራው! ከጉልበቴ ሸብረክ ብዬ እጅ ነሥቻለሁ! የሳትሁትን ነገር አመጣኸው አባቴ ወይራው! በል ነገ ሴቶች ጋር መክረን እንወስናለን:: ፈጥኜ በመወሰኔ ይቅርታችሁን አትንፈጉኝ::" ብለው ቀለሙ ተፈሪ ይቅርታ ከጠየቁ በኋላ ጉባኤው በይደር ተያዘ:: ጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ ወደ ቤታቸው ተበተኑ::





## ፫

ስንብት

በትኔው ሊቅ በኩል ደብዳቤው አልቆ ስንብቱ ሊደረግ ተቃርቧል:: ሊቁ ፋሬስም የመጨረሻውን ስንብት ሊባርኩ በተዋነይ ደሴት ተገጭረዋል:: ታሪኩና ገሞራው በቀኝና በግራ ሰቡራኬ ተሰልፈዋል:: ሊቁ ከሁለቱ ደቀ መዛሙርት መካከል እንደተሰየሙ ወደ ሰማይ ቀና አሉ:: በረከት አሳድርባቸው ብለው የሰማዩን አምላክ እየጠየቁ ነበር:: ወደ ላይ ቤት ቀና እንዳሉ ከሕዋው ላይ አፈጠጡ:: ጊዜው ሌሊት ነበር:: በዛሬው የጸደይ ሰማይ ጨረቃ የለችም:: ሌሊቱ ጽልማሞት ነበር:: ያንን ተከትሎ ሌሊቱ ከበድበድ ብሏል:: የጎንጅ ቀበሌ በጽልመት ስለ ተወረሰ መጨውን ሲያል ያስንቃል:: ላሞቹ ተራክበው ጨርሰዋል:: የእረኞች ዋሸንት ግን ጨለማ ለብሶ እየተንቆረቆረ ነው:: ከላም በረት ተመስገው የሚያድሩ እረኞች እንደ ልማዳቸው ድቅድቁን ጨለማ በዋሽንት ዜማ ያማልሉታል:: ከሩቅ ዶክተር ኄርማ ሊቁ ከዘረፉት ቅኔ ውስጥ ድንቅ ድንቅ ምሥጢር ያለውን ከቅኔ ቤቷ ጎጆ ቁጭ ብሎ ሲከልስ ይሰማል:: ሊቁ ከስንብቱ በፊት ረጅም ገለጣ ጀመሩ::



Scanned with CamScanner

"ለተዋነይ ጥበብ የመረጥኳችሁ ከልቤ ነው:: ማንም አስገድዶኝ አይደለም:: ከደጋ ከቆላ እየመጡ ስንቶች ከእግሬ ሥር ወድቀው ነበር:: ዳሩ ግን ጥበብ ለመጣው ሁሉ አትሰጥም:: ትልቅ ልብ ትመርጣለች:: ከሰው ሰው መርጦ ማውረስ ደግሞ የአበው ወግ ነው:: እኔም እናንተን ስመርጥ ምክንያቴ ብዙ ነው:: እሱን ወደ ፊት ከስዉሩ የጥበብ ዓለም ትረዱት ይሆናል:: ለጊዜው በደፈናው ለተዋነይ ጥበብ ተመርጣችኋል:: እንኳን ደስ አላችሁ::" ስሜታቸውን ሲያነቡ ወደ ገሞራው ቀና አሉ:: ገሞራው በፍሥሓ ተሞልቶ ስሜቱን በመወድስ ለመግለጽ ከተቀመጠበት ብድግ አለ:: አመድረፍ ሲል አባራው ቦለለ:: ቀጥሎ እንደተሰመደው መወድሱን ሲገጨው ዐይኖቹን ሲያስለመልም

"ተወው! ተወው! ዘመኑ የቅኔ ዘመን አይደለም:: የውዳሴ ዘመን አይደለም:: ወደፊት የመልእክ-ሞትን መግቻ ካገኛችሁ ቅኔውን አብረን እንዘርፈዋለን:: መወድሱን እናወርደዋለን ተውው! ተውው! ንሣ ንሣ! ታሪኩ ገልግለው፤ አስቀምጠው:: የእሱ ነገር እንዲህ ነው:: የክረምት ማዕበል ይመስል ደርሶ ይገነፍላል:: እንኳን ውኃዋን ጨምሮበት ይቅርና ድሮም አውቀዋለሁ:: መወድስ ለመዝረፍ ሲነሳ ልቡን ወሰድ ያደርገዋል:: በልጅነቱ አብሾውን እስከ መደቆሻው ሳይጠጣው አልቀረም መሰለኝ:: ንሣ አስቀምጠው::" አሉ ሊቁ::





ታሪኩ አፉፍ ብሎ ተነሥቶ ወገቡን ጭምቅ አድርጎ አስቀመጠው:: መወድሱ ከጉሮሮ ደርሶ ሲመለስ ገሞራው በላብ ተዘፈቀ:: ልማዱ ነው:: ሲበላ ሳይሆን መወድስ ሲዘርፍ ክብ ፊቱ በላብ ይጠመቃል::

ተረጋግቶ ከተቀመጠ በኋላ ግን ለሊቁ በጥንቃቄ መልስ መስጠት ጀመረ::

"የኔታ ከአሁን በኋላ አልዋሽም:: ማርያምን! አልዋሽም! ውሸት የሰይጣን ነው:: ጓደኞቼም እንደሚገምቱት ርስዎም እንደጠቀሱት እኔ አብሾ ጠጥቼ አላውቅም:: ከቶም እርስዎስ መደቆሻውን ጨመሩበት! አንዳንድ ሰዎች ብቻውን አብሾ ሳይሆን እስከ መደቆሻው እንደጠጣሁ በቀልድ መልኩ ሲናገሩ እሰማለሁ:: እኔ ግን መደቆሻው ቀርቶ አብሾ በተደጋጋሚ በአፌ ዞሮ አያውቅም::" አለ ገሞራው ስንብቱ ሊደረግ ጥቂት ሲቀረው::

ታሪኩ ቀበል አድርጎ "ታዲያ ለቅኔ ዘረፋ ስትነሣ በላብ የምትጠመቀው ለምንድን ነው? ድሮ እንዲያውም መወድስ ስትዘርፍ ትወድቅ ነበር:: በቅኔ አደባባይ ሦስት ጊዜ እንደወደቅህ አውቃለሁ:: እኔ ብቻ ሳልሆን ሀገር ያውቅልኻል:: ልትወድቅ ቅጽበት ሲቀርህ እንዴት እንደምትረበሽ አስታውሳለሁ:: መጀመሪያ መውደቅ የጀመርህ

ቀን የሚጥል በሽታ ያለበት መስሏቸው ትልልቅ ሰዎች ከንፈራቸውን እየመጠጡ አዝነውልኻል። ጠላቶችህ ይህንን ተጠግተው ከቅኔ አደባባይ ገፍተው ሲያወጡህ ሩቅ ሄደዋል። አንተ ግን ያንን ሁላ አልፈህ ከዚህ ደረስህ። በዚህ አጋጣሚ እንኳን ደስ አለህ። የሥነ ልቦናውን ጫና ተቋቁመህ ከዚህ በመድረስህ በድጋሜ እንኳን ደስ አለህ። ከፊትህ መቆም የተሣናቸው ድኩማን ከቅኔው ዐውድ ገፍትረው ሲያወጡህ ሲታገሉህ የሚጥል በሽታ እንደ ሌለብህ አስመስክረህ ድጋሜ ወደ መወድሱ ዐውድ ብቅ ብለኻል። አሁን ደግሞ የተዋነይን ውኃ ጨመርህበት። መወድሱ እጥፍ ተገልጦልኻል። እንኳን የተዋነይ የቅኔ አማልክት ታረቁህ።" አለ ታሪኩ። ገምራው በደስታ ተውጦ በዐይኑ ትኩስ እንባ እየፈሰሰ የታሪኩን ጉንጭ ሳመው።

ታሪኩም አጻፋውን እየመለሰ "ጥያቄዬን ሳልፈጽም መሳም የለብህም። መወድስ መዝረፍ ስትጀምር ደጋግመህ ወድቀኻል። ይህ የጤና አይደለም። የምር እናገራለሁ ካልህ እግረ መንገዱን መልስልኝ?።" አለ ታሪኩ።

"እርግጥ ነው ልጅ እያለሁ ዘኢያገድፍ ቢጤ ወስጃለሁ። ያ ግን የሚያሰክር መድኃኒት አይደለም። የጠጣሁት ራሱ በሰኔ ወር መጀመሪያ ነበር። አሁንም ሰኔ ሲገባ ሲገባ መወድስ





ዝረፍ ዝረፍ ይለኛል። የሰኔ ወር ደግሞ በኢትዮጵያ አቆጣጠር የጸደይ ወር ፍጻሜ ነው።

እንደሚታወቀው የፀደይ ወር፣ ወርኀ ሙቀት አይደለም። የቅዝቃዜ ወር ነው። በዚህ ወር የወሰድሁት መድኃኒት ሰውነቴ ሲቀዘቅዝ የሚያነቃቃ መድኃኒት እንጂ አብሾ እስከ መደቆሻው ሊባል የሚችል አይደለም። መቼም የቤቴን ገመና አንተ ታውቃለህ። በዚህ ቅኔ ቤት አብረን ክፉ ደጉን አሳልፈናል። አንድም ቀን ግን የአብሾን ወሬ አንሥተን አናውቅም። ከቅኔ ዘረፋ በቀር ለአስማትም ሆነ ለምትሐት ጊዜ ሰጥተን አውርተን አናውቅም። ዓለም ዘለዓለም ወሬአችን ስለውኃዋ ነበር። እነሆ ጨለጥናት። እንደማር ወለላ ተቋደስናት። ራሷ አብሾ ብትሆን ኑሮ አሁን ሁላችንም በስካር እንዘረር ነበር።" ካለ በኋላ ቅኔ ሲዘረፍ የወደቀባቸውን ዕለታት ለአፍታ አሰባቸው። መጀመሪያ የወደቀው ልቅሶ ላይ ነበር። ቅኔ ሲዘርፍ ድንገት ወደቀ። ያን ዕለት ቅስሙ ተሰበረ። ከሊቃውንት ፊት ላብ በላብ ሆኖ ከእግራቸው ሥር በጥይት እንደተመታ ሲንደባለል መላ አከላቱ በላብ ተዘፈቀ። ሌሊት እንቅልፍ እምቢ አለው። ያን ሌሊት ነበር ተስፋ ቆርጦ ከጎጆው በር ላይ ተቀምጦ ሽራፊዋን ጨረቃ እያየ ሲያለቅስ ያደረው።

"መውደቅ የጀመርሁት ከቅርብ ቀን ወዲህ ነበር። መንሥኤውን በትክክል አላውቀውም። ከመሬት ተነሥቶ የመጣብኝ ጣጣ ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ የወደቅሁት በጸደይ ወር ነበር። በጸደይ ወር አንድ ሊቅ አረፉ። ባለ ውለታዬ ነበሩ። ቅኔው ለእኔ ተሰጠ። ቅኔውን ስጀምር ግን ውስጤ ጥሩ አልነበረም። ውስጤን ደስ ሳይለው መወድሱን ጀመርሁት። መወድሱን ከሥር ስመዘው የታዳሚው ዐይን በገላዬ ፈሰሰ። የሊቃውንቱን ቀልብ ሰብስቦ የመያዝ ተሰጥዎዬን በትክክል ተጠቅሜበት ነበር። ዳሩ ግን በቅኔ ዘረፋው ብዙ አልገፋሁበትም። ሁለት ሦስት መወድስ እንደ ወረወርሁ ላብ በላብ ሆንሁ። ከደቂቃዎች በኋላ ራሴን ከመሬት አገኘሁት። ለመጀመሪያ ጊዜ በአደባባይ ወደቅሁ ማለት ነው። ሊቃውንቱ በትካዜ አፋቸውን ያዙ። ወዳጆቼ አዘኑልኝ። ጠላቶቼ ተሳለቁብኝ።" ብሎ ትንሽ ካዘነ በኋላ

"እግዚአብሔር ይመስገን። አሁን ያ ሁሉ የለም። ይልቁንስ እኔ ለዝና የወደቅሁ መስሏቸው ቅኔ ሳይሠምርላቸው ሲቀር በየቅኔ መዘረፊያው የሚወድቁ ተከታዮችን አፍርቻለሁ። በዚህ የኩሽት አብነት ሁኛለሁ። በተለይ አዲሳባ መውደቁ እንደ አብነት ተወስዷል አሉ። የአዲሳባ ባለቅኔዎች አማረልን





እያሉ ቅኔ ቆጥረው ሲቀኙ እንደሚወድቁ እሰማለሁ። በተለይ አንዱማ መወድስ መዝረፍ ጀምሮ ቅኔ እምቢ ሲለው ከሕዝብ ፊት ወድቆ ሊቃውንቱ ተሳለቁበት ሲሉ ሰምቻለሁ።" አለ ገምራው።

"ቅኔው ምን የሚል ቅኔ ነበር?" አለ ታሪኩ "እረ ተወው! ከቅኔ ቁጥር የለውም።።" ካለ በኋላ ቅኔውማ

"ለጥበብ ሀገሩ አኮኑ ዋሸራ"

የሚል ቁንጽል ቅኔ ነው። ግእዙ ይተርጎም ቢባል ያስቃል። "የጥበብ ሀገሯ ዋሸራ" ናት ማለት ነው። የጥበብ ሀገሯ ዋሸራ ብትሆንም በቅኔ መንፈስ የሚጥል ቅኔ ግን አልነበረም። ባለ ቅኔው ግን ኩሽት ነፍሱ ስለሆነ እንደ ገምራው ስወድቅ ቅኔ የሚሠምርልኝ መስሎት በዚህ ቁንጽል ቅኔ ወደቀ ሲሉ ሰምቼ ስቄአለሁ። ይህ ደግሞ የተፈጸመው ግእዝ መናገር ብቻ ቅኔ መስሎ በሚቆጠርባት በመከረኛዋ አዲሳባ ነው። መቼም ያቺ አዲሳባ "ቅኔና ጠላ" ወጥቶላት አያውቅም። ቅኔና ጠላ የገጠር ሀብቶች ናቸው። በእርግጥ አሁን አሁን እንጀራም እምቢ ብሏታል። ከእንጀራዋ ባዕድ ነገር ይጨመርበታል። የጣውላ ፍቅፋቂ ጋግራ የኮሶ አረቂ ትጨምርበታለች። ጠላ የሚባለውም አንቡላና አተላ ነው። እንደገጠር ጠላ የዶሮ ዐይን የመሰለ ጠላ አይደለም። ቅኔ

የሚባለውም ግእዝ መናገር መቻል ብቻ ነው። ሰምና ወርቁ ተሰርዟል።" ካለ በኋላ ወደ ራሱ ታሪክ ተመለሰ።

"እኔ በጸደይ ወራት የቀመስሁት "ዘኢያገድፍ" አለ። ያለፈውን ቀለም በአእምሮ ቀርፆ የሚያስቀር የሚመጣውን ቀለም የሚገልጥ ፍቱን መድኃኒት ነው። እሱ ከደሜ ጋር ተዋሕዷል። ውስጤን ረብሾት ግን አያውቅም። መውደቁም መድኃኒቱን ተከትሎ የመጣ አይደለም።" አለ ገሞራው።

"ገባኝ! ገባኝ! ዘኢያገድፍ ያቀመሱህ ሰው በትክክልም ትልቅ ሰው ነበሩ።" አሉ ሊቁ ከአንደበቱ ቀበል አድርገው።

"ትልቅማ ትልቅ ናቸው። ዳሩ ግን አብሾ እስከመደቆሻው የሚግቱ አልነበሩም። መድኃኒቱም ሰውነት ሞቅ ከማድረግ ያለፈ ሌላ ትርጉም አልነበረውም። ለእኔ ያደረጉትን ለማንም አስኳላ ተማሪ ሲያደርጉ አይቻለሁ። እኒህ የአስኳላ ተማሪዎች ግን መወድስ ሲዘርፉ አላየሁም። ልዩነት ከዚህ ይጀምራል።" ገሞራው ቀደም ሲል በፀደይ ወር መድኃኒት የሰጡትን ሊቅ በትዝታ አሰባቸው። እሱ ፊደል ሲቆጥር እሳቸው አዛውንት ነበሩ። ኋላ ላይ እንደዋዛ ወጥተው ቀሩ። ስማቸው ሳይቀር ትዝ አለው። የኔታ ይልቃል ነበሩ።" ገሞራው መምህሩ ይልቃልን አስታወሳቸው። በሁሉም ላቅ ያሉ የጥበብና የቀለም ሊቅ ነበሩ። ለአስኳላ ተማሪዎች





ተራውን አድርገው ለገሞራው ግን የተሻለ መድኃኒት እንደሰጡት የሚያውቁ ይልቃል ብቻ ነበሩ። ገሞራው ግን ከአስኳላ ተማሪዎች እኩል የሰጡት እንጂ የተለየ ነገር እንደ ሰጡት ጠርጥሮ አያውቅም።

"አዎን! ያን ጊዜ ልጅ ስለሆንህ ይህ ሊገባህ አይችልም። እሳቸው ግን የጸደይ ወርን የመረጡት አንተን ለመጥቀም ብለው ነው። አየህ? አንዳንድ ሊቆች እንዲህ ዐይነት ምሥጢር ለልጅ ልጅ ሲተርፉ የፀደይን ወር ይመርጣሉ። ጸደይ ደግሞ የተመረጠ ወር ነው። በጋ የደረቀው ሁላ በፀደይ ወራት ነፍስ ይዘራል። ወርኀ ጸደይ ቀላል ወር አይደለም። ምርጥ ወር ነው። ወሩም የጥበብ ወር ነው። የልጆች ልቦና እውቀት የሚከትበት ወር ነው። ቀደም ያሉ የሀገራችን ሊቆች አስኳላ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወርኀ ፀደይ የፈተና ወር ይሁን ብለው የወሰኑትም ከጸደይ ወር እሳቤ ተነሥተው ነው። አሁን ድረስ ያ ወግ እንደቀጠለ ነው። የአስኳላ ተማሪዎች ከመስከረም እስከ ሰኔ ተምረው በሰኔ ወር የዓመቱ መጨረሻ የሆነውን ሀገራዊ ፈተና ይወስዳሉ። ይህ ሲወሰን በዘፈቀደ የተወሰነ አይደለም። የፀደይ ወር በሊቆች ቀመር ተቀምሮ ነው። በዚህ ወቅት የሰው ልጅ አእምሮ ይኀለምሳል። የሰማውን ይሰበስባል። ወሩም አስተጋባኢ ወር ነው። ነጮች ሳይቀር ወሩን ያመልኩበታል።

የአይሁድ ሲታውንት ወርን-ሸዊት ሲሉ ይጠሩታል። የእሸት ወር ማለታቸው ነው። ወሩ በአይሁድ ሲታውንት ቀመር የእሸት ወር ነው። አዲስ እሸት ይቀምሱበታል። ዓመት ዓመቱን ድገመኝ ሲሉ ተምኔታቸውን ይገልጡበታል። ይህንን ወቅት የኢትዮጵያ ሊቆችም ጠንቅቀው ያውቁታል። የጥበብና የዕውቀት ወር ነው። እስኪላ ተማሪዎች ሙሉ በጋ ተምረው የመጨረሻውን ፈተና ይወስዱበታል። የጨረሱ ደግሞ ይመረቁበታል። ስለዚህ ለአንተም ይህ ወር ተመርጦልህ ነበር ማለት ነው።" ካሉት በኋላ የጸደይን ወር ምሥጢር ገታ አድርገው

"ለማንኛውም አብሾ እስከ መደቆሻው ያልሁት ስቀልድ ነው። አንተ የዚያ ሰው አይደለህም። አብሾ እስከመደቆሻው የወሰዱ ሰዎች ጠባያቸው ድፍርስ ነው። ቶሎ ቶሎ ይቆጣሉ። ፈጥነው ይወስናሉ። ፈጥነው ውሳኔአቸውን ያፈርሳሉ። አንተ ግን እንዲህ አይደለህም። የተረጋጋ አእምሮ አለህ። የተረጋጋ አሳቤ ትፈጥራለህ። ከሌሎች አብልጬ የምወድህም ለዚህ ነው።" ብለው ቀልዱን እያስተባበሉ ገሞራውን አረጋግተው ወደፍሬ ነገሩ ሊገቡ ሲሉ...





"ለመሆኑ ግን አብሾ እስከ መደቆሻው ይጠጣል? መደቆሻውኮ ልሙጥ ድንጋይ ነው?።" አለ ታሪኩ ቢጫ ፈገግታ ፈገግ እያለ። ገሞራው ተደርቦ ሳቀ።

"እኔም ስቀልድ ነው። በእርግጥ አንዳንዱ በቀለም ሊቅ፣ በጠባይ ነጭናጫ ሲሆን አብሾውን እስከ መደቆሻው ተግቶታል ይባላል። ንግግሩም ብሒል ነው። በጃንሆይ ዘመን ከነበሩ ሊቆች ቀዳሚው ሊቅ መደቆሻው ይባሉ ነበር።" አሉ ሊቁ ፋራስ ፈገግ ብለው።

"ማናቸው እሱ በጃንሆይ ዘመን የነበሩ ሊቅ? አባ ሐና? ወይስ ሌላ ሊቅ?" አለ ገሞራው።

"በጃንሆይ ዘመን ሊቆችም ውድቆችም ነበሩ። ውድቆች የቤተ መንግሥቱ ጠጅ ባራኪ ሲሆኑ ሊቆች ግን ከጃንሆይ ጋር መቀጠል ያልቻሉ ናቸው። ጃንሆይ ሰማይ አይታረስ ንጉሥ አይከሰስን ሲደጋግሙ ከቤተ መንግሥት ወጥተው መንነዋል። ገዳም ተቀላቅለዋል። ከእኒህ ሊቆች መካከል መደቆሻው ገብረ ዮሐንስ የውስጥ አማካሪ ነበሩ።" ሲሉ ታሪኩን ከቤተ መንግሥት ሳቡት። ሕሊናቸው ወደ ገብረ ዮሐንስ ገሰገሰ። እናም አከሉበት።



Scanned with CamScanner

“መደቆሻው ገብረ ዮሐንስ የጃንሆይ የውስጥ አማካሪ ነበሩ:: ፊት ለፊት መናገር የሚወዱ እውነተኛ መምህር ነበሩ:: ጃንሆይ ሲያጠፉ ፊት ለፊት ይነግሯቸዋል:: በአደባባይ ይዘልፉቸዋል:: ይህ ዐመላቸው ከጃንሆይም ሆነ ከቤተ መንግሥት ሊያኖራቸው አልቻለም:: ጃንሆይ ሲስቱ በነገር ይደቁሷቸው ጀመር:: አባ ሐና አሜን አሜን ሲሉ መደቆሻው 'እንዲህ ግን አይነቱን ነገር መጽሐፍ ይከለክለዋል:: ታሪክ ይደፈጥጣል:: የነገ ልጅ ይወቅሰናል:: የገዛ ውሻችን ከቤተ መንግሥት ያስወጣናል:: መጻኢው ዘመን የቤታችን ውሻ የሚሰለጥንበት ዘመን ነው' እያሉ የደርጉን መምጣት በቅኔና በአሽሙር መናገር ጀመሩ:: ይህ ሰብእናቸው ከአባ ሐና በተቃራኒ አቆማቸው:: ጥቂት ቆይቶም ከቤተ-መንግሥት አስወጥቶ ገዳም ጣላቸው:: ገዳም ከገቡ በኋላ መናገር እንዳላቆሙ በተደጋጋሚ ሰምቼ አውቃለሁ:: እኔም ሁለት ሦስት ጊዜ ገዳም ሂጄ ጠይቄአቸው ነበር:: ከቤተ መንግሥት ወጥተው ቀጥታ ማኅበረ ሥላሴ ገቡ:: በዚህ ገዳም ከሰኞ እስከ ዓርብ ድረስ ረድእ ሆነው ሲያርሱ ሲቆፍሩ ይውላሉ:: ቅዳሜ ቅዳሜ ለገዳማውያኑ መጽሐፍ ያስተምሩ ነበር:: በዚህ ሲኖሩ ከዕለታት ባንድ ቀን ደብረዳሞ ገዳምን ሊሳለሙ ሄዱ:: በዚያ ጥቂት ዓመታትን አሳልፈዋል:: ያን ጊዜ ነበር እንግዲህ





አባ ገብረ ዮሐንስ፣ መደቆሻው የተባሉት::" ብለው ሳቁ:: ታሪኩና ገምራው አብረው ፈገግ ካሉ በኋላ

“እንዴት ግን መደቆሻው ተባሉ?" አሉ ሁለቱም በጋራ

“በገዳሙ ውስጥ ቀኖና ሲጣስ አይተው ያለምንም ፍርሐት መናገር ጀመሩ:: የደብረ ዳሞ መነኮሳት ድፍረታቸውን አይተው ይህስ አብሾውን እስከ መደቆሻው ነው የተጋተው ሲሉ ነቀፉ ቢጤ ጣል አደረጉባቸው:: ከዚያ ወዲህ መደቆሻው ገብረ ዮሐንስ ተብለው ቀሩ:: የስሙ አመጣጥ ይኸው ነው:: የመደቆሻው ታሪክ ከዚህ ይበቃል:: ወደ ራሳችን ሥራ እንግባ::" ብለው ትእዛዝ ከሰጡ በኋላ

“ያላችሁት በተዋነይ ደሴት ውስጥ መሆኑን አትርሱ:: ነገ ከዚህ የላችሁም:: ወደ ተዋነይ ዓለም ትቀላቀላላችሁ:: ቀደም ሲል በዚህ ስፍራ አያሌ ሊቆች ነበሩበት:: ዛሬ ላይ ሁሉም የተዋነይን ዓለም ተቀላቅለዋል:: ወደ ስዉሩ ዓለም ነው የምልካችሁ:: ቀደምቱ ወደ ተዋነይ ዓለም የተቀላቀሉት ተገድደው አይደለም፤ በፈቃዳቸው ነው:: እኒህ ሁሉ ከተዋነይ ጥበብ አንዳንድ ቀስመዋል:: ወደዚያው ትሄዱ ዘንድ መርቄ ልሸኛችሁ:: በሉ ብድግ በሉና ቡራኬ ተቀበሉ:: መርቄ ልሸኛችሁ::" እንገታቸውን ዘንበል ዘንበል አድርገው ከተመረቁ በኋላ ከታብር ውኃ ቀድተው ሰጧቸው::

"በሉ ከስዉሩ ዓለም ስትደርሱ ውኃውን ተቋደሱ። በዚህ ጊዜ በስዉሩ ዓለም ያሉ ጠቢባን ይከሰቱላችኋል። ሰላም ግቡ። መንገዳችሁ በጥንቃቄ ይሁን። ከመንገድ ሞት እንዳይኖር ተጠንቀቁ። ስትደርሱ ይችን ደብዳቤ ለቀለሙ ስጡልኝ። ቀለሙ ተፈሪ የቅኔ ቤት ጓደኛዬ ነበር። አሁን ላይ ከደቂቀ ተዋነይ አንዱ ሁኗል።" ብለው የተጠቀለለ ደብዳቤ ሰጥተዋቸው የመጨረሻው ስንብት ተጠናቀቀ።

ገሞራውና ታሪኩ ተሰናብተው በደረቀው ሌሊት ጉዞ ጀመሩ። ያን ቀን በጎንጅ ደብረ ጥበብ ጨረቃ አልነበረችም። ደረቅ ሌሊት። ጠፍ ጨረቃ። የጥበብ ጉዞ!! መልአከ ሞትን ለማሰር የሚደረግ መሸቀዳደም!!

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)





# ፯

### በሩ ተከረቸመ

በስዉሩ ዓለም ሰማይ ሥር ዱር አራዊቱ ይዘምራሉ። በስዉሩ ዓለም ሰማይ ሥር ዱር አራዊቱ ይዘምራሉ። ከርታታ ኮከቦች በየጉራንጉሬው ያሉ ንቦች ህም ህም ይላሉ። ከርታታ ኮከቦች ደቂቀ ተዋነይ ለሁለተኛ ጊዜ ለጉባኤ ተሰይመዋል። በስዉሩ ዓለም ያሉ ሴቶችም በዛሬው ጉባኤ አብረው ታድመዋል። የዛሬው አፈ ጉባኤ ደቀኛው ነበሩ። ጉባኤው እንደ ተጀመረ በቋንቋቸው በግእዝ መናገር ቀጠሉ።

"እኛ ጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ ለዚህ ጉዳይ ስንቀመጥ ሁለተኛ ቀናችን ነው። ባለፈው ዓርብ መስከረም አንድ ቀን ተሰብስበን ነበር። እናንት የስዉሩ ዓለም ሴቶች ለወንዶች ቤዛዎች ናችሁ። የሞትን ደካማነት የተረዳነው በእናንተ በኩል ነው። የእኛ ከርታታ ኮከቦች ቤዛ፣ የስዉሩ ዓለም ከዋክብት እናንት ሴቶች ናችሁ።" ብለው የሴቶችን ልብ በውዳሴ ሰማይ ከሰቀሉ በኋላ ቀጠሉ።

"ባለፈው ዐርብ እኛ ደቂቀ ተዋነይ ተጀምሮ ያልተቋጨ ሐሳብ እንሥተናል። እሱ ምን መሰላችሁ? የስዉሩ ዓለም ምሥጢር መኻል ሀገር እንደጉድ መወራት ስለጀመረ ወደዚህ ዓለም የሚመጡ ሰዎች ተበራክተዋል። ከዛሬ ጀምሮ ወደ

ስዉሩ ዓለም የሚቀሳቀሱ ሰዎች መመረጥ አለባቸው:: አስኪላ ተማሪው ሁሉ እየመጣ ስዉሩን ዓለም እየሰለለ ስለሆነ በራችንን እንዝጋ:: ስዉሩ ዓለም ይከርቸም ብለን ነበር:: ነገር ግን የዚህ ዓለም ቤዛዎች እናንተ ስለሆናችሁ ለብቻ መወሰን ስለሌብን በይደር ይዘነዋል:: ጉባኤው የእናንተን አንደበት ይፈልጋል::" ብለው ወደ ስዉሩ ዓለም ሴቶች አማተሩ:: ሴቶች ከቅጠሉ ጋር ቅጠል መስለው በየዛፉ ተሸጉጠው በማድመጥ ላይ ነበሩ::

"እኸ! በሉ እንጂ የእኛ ቤዛዎች!" አሉ ደቀኛው ርስ በርሳቸው እየተያዩ ዝም ስላሉ::

በመኻከል አንዷ ሴት ከቅጠሉ ሥር ተወሽቃ በግእዝ ቋንቋ መናገር ጀመረች::

"በኀቤየ ሠናይ ውእቱ ዝ ጉባኤክሙ ወዝ ውሳኔክሙ:: እመኒ ፈቀድክሙ ዕፅዉ አናቅጺሃ ለደቅ ዓለመ ጠቢባን ዘእደው ወዘአንስት ወለእለ አልቦሙ ልብ እደው ኃያላን እለይነብሩ ምስሌነ::" ካለች በኋላ ጠቢባኑን እጅ ነሥታ ተቀመጠች:: ደቀኛው ለወይራው ተረጎሙላቸው:: ቀላል ዘይቤ ነው:: ይኸውም "በእኔ በኩል ጉባኤው ሠናይ ጉባኤ ነው:: ውሳኔውን ተቀብያለሁ:: ከፈለጋችሁ የልበ ቢሶችን ጨምራችሁ የጠቢባንን በር ዝጉ" ማለት ነው:: ሴቷ





ስትናገረው ከባድ ቢመስልም ቀላል ቃል ነው ሲሉ ደቀኛው ለወይራው ተረጎሙላቸው:: እንደ ቄስ ደፈርሻ ግእዝ እምቢ ብኂቸው የቀረ ሰው ቢኖሩ ወይራው ናቸው:: ግእዝ ለመናገር መፍትሔ-ልሳናት ጭምር ወስደው ነበር:: ልሳናቸው ሳይፈታ ምላሳቸው ግእዝ ቋንቋ ሳይደፍር ቀረ:: ቀጥሎ ሁለተኛዋ ሴት በግእዝ ቋንቋ ለመናገር ቃጭል ድምጧን ስታቃጭል የእለቱ አፈ ጉባኤ ደቀኛው አቋረጣት::

"ተይ ተይ! ተይ እምዬ! ከጉባኤው ውስጥ ያለን ሰዎች በቋንቋ በኩል ኻንጉርጉሮች ነን::" ሲሉ ወይራው በደስታ ፈገግ አሉ:: በወጥመድ እንደተያዘች ጃርት ከመካከል ቁጭ ብለው ቁልጭ ቁልጭ ሲሉ ነበር:: ፊታቸውም በከፊል የቄስ ደፈርሻን ፊት ተላብሷል:: ደቀኛው የሰው ችግር ፈጥኖ ይገባቸዋል:: ከግእዝ ቋንቋ በቀላሉ ገላገሏቸው:: እንስቷ ባማርኛ ቀጠለች::

"ከመኻል ሀገር የሚመጡ ወንዶች ይቅሩ ማለታችሁን ወድጀዋለሁ:: በታሪክ እንደምናውቀው ተዋነይ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ጥበብ ከተማረ በኋላ ትኋን ሆኖ ተመለሰ::

በዚህ የተነሣ ከተዋነይ ጋር ፍቅር የነበራት ሴት ተዋነይን ተከትላ ከስዋሬው ዓለም ወደመኻል ሀገር ከሄደች በኋላ አልተመለሰችም::



Scanned with CamScanner

ተዋነይ እንደማያገባት ስታውቅ ከኀብስተ መናው አልበላም ብላ ዐፈር በላች፡፡ ተዋነይም ቢሆን በእሷ በኩል ሰሙ ተሰብሯል፡፡ በስዉር እየመጣች ታናግረው ስለ ነበር በወቅቱ ተዋነይ ከሴት ዛር ጋር ግብረ-ሥጋ ይፈጽማል ተብሎ በሐሜት ሥጋው ተከተፈ፡፡ የተዋነይ ሚስት የዛር ውላጅ ነበረች የሚባለው ልብ ወለድ አሁን ድረስ ይወራል፡፡ ያች ሴት ግን የዛር ውላጅ አልነበረችም፡፡ ከእኛው ከስዋሬው ዓለም ወጥታ በፍቅር የኮበለለች ቆንጆ ነበረች፡፡ አፈር በላች፡፡" እንባ እየተናነቃት ቀጠለች፡፡

"ሌላው ከአያሌ ዓመታት በፊት ከዐራት ዐይናው ጋር የመጣው የዋሸራው ኪነ-ጥበብ ነበር፡፡ መናውን ከቀመሰ በኋላ ወደመኻል ሀገር ሊመለስ ወደደ፡፡ ይች እኅቴ በመሰውር ሰውራ ዋሸራ አድርሳው ተመለሰች፡፡ ከዚያ በኋላ ወንድ ልጅ እንደቡዳ ፈርታ ቀረች፡፡" ካለች በኋላ ወደራሷ የሕይወት ገጠመኝ ዘው ብላ ገባች፡፡

"እኔ ራሴ አፍቅሬ እንደነበር ታውቃላችሁ፡፡ ከዛሬ ዐሥር ዓመት በፊት አንድ የቅኔ ተማሪ መጣ፡፡ ሳየው ወደድሁት፡፡ ዐይነ ኮሉ የቀይ ዳማ ነበር፡፡ በፍቅር እብድ ብዬ የጣቴን ቀለበት ሰጠሁት፡፡ እንደ እኔ ተሰወረ፡፡ ወደ ሴቶች ስዉር





ዓለም ወሰድሁት፡፡ ተከተለኝ፡፡ የአንገቴን ሐብል ከአንገቱ ሳጠልቀው ከሰማይ የወረደ መልአክ መሰለኝ፡፡

ከኀብስተ መናው በቀር መላ ጥበበ ተዋነይን አስተማርሁት፡፡ ልቤ በፍቅር ጥልጥል ብሎ ስለነበር የሰወርሁት ነገር አልነበረም፡፡ በኋላ ቀለበቴን መልሶልኝ ወደ ዳንግላ ተመለሰ፡፡ ተሰውሬ እግር እግሩን ተከትየው ዳንግላ ድረስ ወረድሁ፡፡ በዚያም ሁለት ሳምንት ድረስ እሱ በገሀድ፣ እኔ በስዋሬ አብሬው ሰነበትሁ፡፡ ባየው ባየው አልጠግበው ስል ከጉልበቱ ተደፍቼ ለጋብቻ ለመንሁት፡፡ ፍላጎቱ ምንኩስና እንደሆነ ነገረኝ፡፡ ውዳሴ ማርያም የደገመበትን ከንፈሩን ስሜው ተመለስሁ፡፡" ካለች በኋላ ጥቂት እንደማፈር ብላ ቀጠለች፡፡ ንግግሯንም ወደ ግእዝ ቋንቋ ለወጠችው፡፡ ገዳማዊው ወይራው እንደ ተቆጡ ዐይታ ነው፡፡ እሷ ስለ ፍቅር ስታወራ ገዳማዊ ወይራው ገጻቸው እንደቁራ ጠቁሮ ነበር፡፡ የፍቅር ታሪኳን ከወይራው ለመሰወር በግእዝ ቋንቋ ቀጠለች፡፡

"የፍቅር ጉዳይ ሆኖብኝ ባመቱ ተመልሼ ወደ ዳንግላ ሄድሁ፡፡ ስደርስ መንኩሶ አገኘሁት፡፡ ከአሁን በኋላ የእኔ መሆን አትችልም፡፡ "እግዚአብሔር ያስፈጽምህ" ብዬ ለመጨረሻ ጊዜ ጉልበቱን ስሜው ተመለስሁ፡፡ ይኸው ለዘለዓለም በድንግልና እየኖርሁ ነው፡፡ ከከንፈሬ በቀር

ድንግል ነኝ፡፡ ፍቅር ደንግሎኛል፡፡ ከእሱ በቀር ፍቅር ገደል ይግባ ብዬ ቀጠልሁ፡፡ እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ ይህ ስዉሩ ዓለም ይዘጋ፡፡ እኛም በስዋሬ ብቻ እንቀጥል፡፡ በክበሮ ከማመስገን በድምፅ ብቻ እናመስግን፡፡ ከዚያ በኋላ ከመኻል ሀገር የሚመጡ የአብነትም ሆነ የአስኳላ ተማሪዎች ተስፋ ቆርጠው ይቀራሉ፡፡" ብላ ሐሳቧን ስትቋጭ ጠቢባኑ ደቂቃ ተዋነይ በጭብጨባ አጀቧት፡፡ ጉባኤው የውስጡንና የገሀዱን ክልኤ ዓለም የሚጠብቁ ሁለት ሰዎች ሹሞ ተለያየ፡፡ ለስዉሩ ዓለም ዐራት ዐይናው ሲመረጡ ለገሀዱ ዓለም ደግሞ ጠቢቡ ሖረ ተመደቡ፡፡ ሁለቱ ሊቆች የስዉሩንና የገሀዱን ዓለም ሊጠብቁ ቃል ገቡ፡፡ ጉባኤው ማንንም ላይቀበል ተስማምቶ ተበተነ፡፡ በሩ ተከረቸመ፡፡





## ፲

ትዝታ ዘጎንደር

"ገባኝ! ገባኝ! ተገለጠልኝ" ሲል ታሪኩ አጨበጨበ፡፡

"ምኑ ነው የተገለጠልህ?" ገሞራው በጭብጨባ እያገዘ ጠየቀው፡፡

"ስዉሩ ዓለም መኖሩን ያመንሁት ከመሬት ተነሥቼ አይደለም፡፡ ይህ የጠቢባኑ ዓለም በኢትዮጵያ ጫፍ ያለ ሀገር እንደሆነ ሰምቻለሁ፡፡ እስከ ዛሬ ስፍራውን በግልጥ የሚናገር ሰው ግን አልነበረም፡፡ በዚህ ስፍራ ያሉ ጠቢባን በጥበብ መልአከ ሞትን ገዝተው የሚኖሩ እንደሆኑ የኔታ ነግረውናል፡፡ በግሌ ግን የሰማሁት ምሥጢር አለ፡፡ እሱ ምን መሰለህ? በየጊዜው የተነሡ የሀገራችን መሪዎች ወደዚህ ዓለም ለመግባት ይሞክሩ እንደነበር የወሬ ወሬ ሰምቻለሁ፡፡" አለ ታሪኩ፡፡

"እረ በማርያም! አትቀልድ፡፡" የሀገራችን መሪዎች ወደዚህ ዓለም ለመግባት ይሞክሩ እንደነበር ሰምቻለሁ ሲለው ገሞራው በድንጋጤ ክው አለ፡፡



Scanned with CamScanner

"ጃንሆይ ወደዚህ ስፍራ በየጊዜው ተመላልሰዋል:: መግባት ግን አልቻሉም:: ጓድ መንግሥቱ ከአንድም ሁለት ሦስት ጊዜ ሞክረው ነበር:: ከጠቢባኑ ዓለም ግን ሊገቡ አልቻሉም:: ሁለቱም ለአካባቢው አርሶደሮች ወፍጮ አበርክተው ተመልሰዋል:: ሌሎች መሪዎችም ደከመውበታል:: የሞት መግቻው በእጃቸው እንዳልገባ ግን ከሞታቸው መረዳት ይቻላል:: አሁን ላይ ከጓድ መንግሥቱ በቀር ሁሉም አርፈዋል:: መንግሥቱም ነገ ማለዳ ተከታይ ናቸው:: የሞት መግቻው በእጃቸው ስላልገባ የተፈጥሮ ሞት ይሞታሉ:: የሞት መግቻው በእጃቸው ገብቶ ቢሆን ሐረሬ አይሄዱም ነበር::" አለ ታሪኩ::

"ከጓድ መንግሥቱ በኋላ የነበሩትንም ያካትታል?" አለ ገሞራው::

"አዎን! እንዲያውም ሰውዬው የተጠቀመው መንገድ ከጠቢባኑ ዓለም የሚያደርስ መንገድ ነበር:: ከጠቢባኑ ዓለም ግን መግባት አልቻለም:: አካባቢውን ግን ለግሉ ከልክሎት ነበር ይባላል:: ወደዚህ ዓለም የሄደ ቀን ተራ ልብስ ለብሶ አልባሌ መስሎ ነበር አሉ:: እንደ ደረሰ ሰው እንዳይለየው ሌላ ሰው መስሎ ነበር:: በኋላ ግን ከኩንፈልና ከዐባይ ዳር ለከብቶቻቸው ሣር ሊያግጡ የመጡ ዘላኖችን ሰብስቦ ንግግር





አድርጓል:: ንግግር በሚደርግበት ወቅት 'ይህ አካባቢ የላም ግጦሽ ሊሆን አይችልም:: ከዚህ ምን አመጣችሁ? አሁኑኑ ለቃችሁ እንድትወጡ' ብሎ ቱግ ሲል እሱ መሆኑ ታውቋል:: በእርግጥ ይህን ንግግር ማንም ሊናገረው ይችላል:: በትክክል የታወቀው ግን ደርሶ ከተመለሰ በኋላ የጠቢባኑ ዓለም ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚጠረጠረውን ክፍል በልዩ ሠራዊት ማስጠበቅ በመጀመሩ ነበር:: ከነጮች በቀር ማንም መግባት እንደ ሌለበትም ትእዛዝ አስተላልፏል:: እስከቅርብ ቀንም ነጮች በዚህ ስፍራ እንደሚርመሰመሱ በትክክል ሰምቻለሁ:: ከዚያ በፊትም ጃንሆይ የሕዳሴውን ግድብ በዚያ በኩል መገደብ የፈለጉት በሰበቡ ስዉሩን ዓለም ለመፈተሽ ነበር:: ሳያሳኩት ሞት ቀደማቸው::" አለ ታሪኩ

ገሞራው እንዳይጠረጥረው ከታብር ተጎንጭቷል:: ታብርን ከቀመሰ በኋላ ደግሞ ውሸት መዋሸት ክልክል እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል:: በሙሉ ልብ እንዳያምነው ማስረጃ አጣ:: በዚያ ላይ አሁን አሁን ስዉር ዓለም ተገለጠልን የሚሉ ሐሳውያን በዝተዋል:: ከባሕል ሐኪሞች እስከ ግልብ ደራሲዎች ስዉር ዓለም የፈጠሩበት ግልብ ዘመን መጥቷል:: በየተራራው ከርስ የተሰወረ ዓለም ተገለጠልን የሚሉ ሐሳውያን ተበራክተዋል:: ሐይቆችን የጨመሩም አሉ:: እነኚህ ግን አንዳች ተጨባጭ ማስረጃ የላቸውም:: የሕዝቡን ቀልብ

ለመስለብ የፈጠሩት ሐሳዊ ፈጠራ እንደሆነ ገሞራው ያውቃል።

"ይህን ያወጋህ ማን ነው?።" አለ ገሞራው በማመንና ባለማመን ዐይን እየተመለከተው።

"የጠቢባኑን ዓለም ምሥጢር የነገሩኝ አንድ ከርታታ ሰው ናቸው። ቅጽል ስማቸው ደቀኛው ይባላል። ሰውየው እንቅልፍ አያውቁም። ሰውነታቸው የደረቀ ቆሽቋሻ ቢጤ ነበሩ። በ1998 ዓመተ ምሕረት ጎንደርን ሊጎበኙ መጡ። ያን ጊዜ ፀሐይ እኩለ ቀን ላይ ለአፍታ ጨልማ ነበር። በዚች ዕለት ነው የመጡት። ያን ጊዜ እኔ ቅኔ ዘራፊ ነበርሁ። በዚች ቀን ፀሐይ ድንገት ድንግዝግዝ ብላ ጠፋች። ጎንደር ለአፍታ በጨለማ ተዋጠች። በቅኔ ቤቱ መኻል ተኮልኩለን ስንደነቅ አፍታ ወሰደብን። ከአፍታ በኋላ እኒህ ከርታታ ሰው ብቅ አሉ። ቋንቋቸው ግዕዝ ብቻ ነበር። ያውም ሾካራው ግዕዝ። ከግዕዝ በቀር ሌላ ቋንቋ አይናገሩም። አመጣጣቸው ጎንደርን ሊጎበኙ ቢሆንም ለምን ይህንን የጨለማ ቀን ጠብቀው እንደመጡ ግን አሁን ድረስ እንቆቅልሽ ነው። ያልተፈታ ቅኔ ስል እገልጠዋለሁ። የጎንደርን አብያተ መንግሥት ሊጎበኙ ሲመጡ የቋንቋ ችግር ተፈጠረ። ከጎንደር አስጎብኚዎች ግዕዝ ተናጋሪ አንድ እንኳን የለም። ሁሉም



የፈረንጅ አፍ ተናጋሪ ብቻ ነበሩ። ለውርርድ ግዕዝ አዋቂ የለም። በእርግጥ ግዕዝ ተናጋሪ ጎብኝም ይመጣል ተብሎ ታስቦ አያውቅም።

ባገድ ወቅት ግን ግዕዝ ተናጋሪ ጎብኝ ብቅ አሉ። የጎንደር አስጎብኝዎች ዐይናቸው ፈጠጠ። አስተርጓሚ ፍለጋ ወደቅኔ ቤት መጡ። ከቅኔ ቤት እኔ ተመረጥሁ። ላስጎበኛቸው ስሞክር ከእኔም ጋር በግዕዝ እንደ ልብ ለመግባባት ትንሽ አዳገተን። እኔ በቀዳማይ እንቀጽ ስጀምር ሰውዬው በንዑስ አንቀጽ ይጀምራሉ። በኋላ ጥቂት ጥቂት ተግባባን። እናም በጉብኝቱ ሰዓት ብዙ ብዙ ጥበብ ነክ ነገር እንደዋዛ ነገሩኝ። በወቅቱ የጥንቆላ መንፈስ መስሎኝ ቸላ አልሁት። ልጅነቴ የጎዳኝ ከዚህ ላይ ነበር።" አለ ታሪኩ ደቀኛውን መልሶ እያሰበ።

"በምን ዙሪያ አውርተውህ ነበር?" አለ ገሞራው እሱም በእኩለ ቀን ፀሐይ የጨለመችበትን ምሥጢር በፀሐይ ቀመር እየመረመረ። ዐውደ ፀሐይን እየፈታ እየቋጠረ።

"ወደ ፊት ኑሮው ይወደዳል። ዐፈር እየተበላ ከሚኖርበት ዛፍ ጠጋ ማለት ይሻላል። ልብሳችን ቅጠል፣ ቁርሳችንም ዐፈር የሚሆንበት ጊዜ ሊደርስ ሦስት ዓመት ብቻ ቀርቶታል ያሉኝ አሁን ድረስ በውስጤ ያቃጭላል። አሁን ኢትዮጵያ

እንደቀድሞው በፍሥሓ መኖር ሲሳናት ሳይ እኒያ ክርታታ ሰው በሕልሜ እየመጡ አብረውኝ ያድራሉ:: ምሥጢሩ ግን አሁን ድረስ ኅቡእ ነው:: ራሱን ደብቆ በውስጤ ይኖራል::" አለ ታሪኩ::

“ልብሳችን ቅጠል፣ ቁርሳችን ዐፌር የሚሆንበት ጊዜ ሲደርስ ሦስት ዓመት ቀርቶታል ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ምሥጢሩ ከዚህ ይጀምር ይመስለኛል?::" አለ ገሞራው::

“ምን አባቴ አውቄ! ሳስጎበኛቸው ሰንብቼ ልንለያይ አካባቢ ከበረሃ የምትኖር አንዲት ዐፌር አለች:: ጥፍጥናዋ የጉድ ነው:: ትኩስ እንጀራ ስትፈልግ እንጀራ አድርገህ ትጋግራታለህ:: ቂጣ ስትፈልግ እንጎቻ አድርገህ መመገብ ነው:: ያችን ዐፌር እየበላህ ታነባለህ:: ከዚያ በኋላ የሆድ ጉዳይ አሳሳቢ አይደለም ብለው ተስፋ ሰጥተውኝ ነበር:: በመጨረሻው ቀን ግን ተሰወሩ::" አለ ታሪኩ ወደኋላ ተመልሶ ፀሐይ በጠራራው ቀን የጨለመችበትን ዓመት እየመረመረ::

“ተሰውሩ? እየቀለድህ ነው?" አለ ገሞራው ደንግጦ::

“እውነቴን ነው:: መሳ ጎንደርን ዘወር ዘወር እያልን ስንጎበኝ የመንግሥት ሰዎች ሲከታተሉን ሰንብተው አንድ ምሽት





ብልኮ ሰፈር በቁጥጥር ሥር አዋሉን:: ደቀኛው ከፊታቸው ተሰወሩ:: እኔ ስድስት ዓመት ታሥሬ ተገርፌ በሕይወት ወጣሁ::" አለ ታሪኩ:: ገሞራው ጥቂት ሲተክዝ ቆይቶ

“ያች ዐፌር በእጅህ ገብታ ቢሆን ኑሮ አሁን የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን የሚለውን ጸሎት አልፈን በደላችን ይቅር በለን እያልን ብቻ መጸለይ ነበር::" አለ::

“ብትክክል!"

ከዚያም ገሞራው አከለበት:: “መቼም አሁን ታብርን ጠጥተናል:: ከፊል እውቀትም አውቀናል:: ያን ዐፌር እንጀራ ሊሆን የሚችልበትን ምሥጢር እንዴት ታየዋለህ?" ገሞራው የማይመለስ ጥያቄ ጠየቀው::

“ምን ችግር አለው ብለህ ነው:: ዐፌሩ የተፈጥሮ ዐፌር ከሆነ እንጀራም ቢያደርጉት ይሆናል:: ቂጣም ቢያደርጉት ድርብርብ ቂጣ ይሆናል:: ለእግዜር ምን ይሳነዋል ብለህ ነው:: ይህን ዐፌር ሲፈጥር ለዚህ ከፈጠረው መሆን ይችላል:: ምሥጢሩ ከተፈጥሮ ላይ ነው::" ታሪኩ ተፈላሰፈበት::

“እስኪ በምሳሌ አስረዳኝ? የዛሬው መምህርነት ያንተ ነው?" አለ ገሞራው

አውቃቸዋለሁ። የደስ ደስ ያላቸው ሰው ናቸው። ከተዋነይ በኋላ ከተሰወሩ ሊቆች አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ።" ብሎ ቀና ሲል የኄርማ ድምፅ አናጠበው። ሁለቱ ታብርን ጠጥተው ወደ ስዉሩ ዓለም ሲገሰገሱ ዶክተር ኄርማ ቅኔ እየዘረፈ ነበሯ።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
Telegram channel





# ፳

ከቅኔ ቤቷ በር

ከቅኔ በኋላ ለጥበብ ልባቸው ቋሟል። በተለይ ከስዉሩ ዓለም ለመግባት ቆርጠው ተነሥተዋል። ገሞራውና ታሪኩ መንገድ ሲጀምሩ ቅኔ ቤቷ በቅኔ እሳት እየነደደች ነበር። ከአስኳላው ዓለም ወደ ቅኔ ቤት ለመጣው ዘመናዊው ሊቅ ኄርማም ቅኔ ሰልጦታል። መወድሱ ገብቶታል። የሰምና ወርቅ መሠረት ጥሏል። ሰምና ወርቁን ከጣለ ቀሪው የቅኔ መንገድ ደግሞ ቀላል ነው። ከፊሉን ደርሶበታል። ያውም በቀላል ቀን። ታች አምና ጀማሪ ነበር። አሁን ግን በአስኳላው ዓለም ዶክተር ሲሆን በአብነቱ ቀለም በኩል ደግሞ ቅኔ ዘረፋ ድረስ ገስግሷል። ያቺን የፀደይ ጨረቃ የመሰለች ፍቅረኛውን ግን የረሳ አይመስልም። ሳቋ፣ ፈገግታዋ፣ እርጋታዋ፣ ጨዋታዋ፣ ስንቱ ይረሳል? ከልቡ በቅላለች። ደረቱ ላይ ራሷን ደገፍ አድርጋ ሽቅብ ወደ ዐይኖቹ እያየች የሳቀቸው ሳቅስ ቢሆን መቼ ይረሳል? የመንግሥተ ሰማያት መፍቻ ቁልፍም አይደለም? እሷስ ቢሆን የገነት አበባ አይደለችም? ይህን ሁሉ ከረሳማ ምኑ ባለቅኔ ሆነው! አይረሳውም። በዚች ምሽት ብቻ ሦስት ዐራት ጊዜ ተስቶት ከአብነት ተማሪዎች ፊት ስሟን አንሥቶታል።



Scanned with CamScanner

ሁለቱ መንገድ ሲጀምሩ እነሆ ያች የምሽት ጨረቃ በደመና ተከልላ ሰማዩ የዲያብሎስን ገጽ መስሏል፡፡ የብርሃን ፍንጣቂ የለም፡፡ የጨረቃ ብርሃን ከሰዎች ዐይን ጋር ሊዋሐድ አልቻለም፡፡ የጨረቃ ብርሃን በጉም ተሰጉሟል፡፡ የአካባቢው ሰዎች በእንቅልፍ ሰጥመዋል፡፡ ከሩቅ ግን የቅኔ ተማሪዎች ድምፅ ይሰማል፡፡ ቅኔ ከሚዘርፉት መካከል የኄርማ ድምፅ ማደ ገመገሙ ድረስ ይተማል፡፡ ኄርማ የነጠረ ዶክተር ቢሆንም ቅኔ ቤቱን ሲቀላቀል ፍቅረኛው ትዝ እያለችው ተቸግሮ ነበር፡፡ አሁን ግን እሷን በልቡ እንደያዘ በቅኔው ገፍቶ ለአቅመ ዘራፊነት ደርሷል፡፡ ፍቅር ቀልብ ይሰልባል የሚባለውን የሥነ ልቦና ዘይቤ ጥሶታል፡፡ ፍቅርና ቅኔን ባንድ ልብ አጣምሮ ይዟል፡፡ “ናርዶስ” ለአፍታ ከውስጡ ወጥታ አታውቅም፡፡ በጨረቃ ድምቀት ትመጣበታለች፡፡ በተለይ በተለይ ከጨረቃ መባቻ ጀምሮ ፍቅር ይጸናበታል፡፡ አእምሮውን ደስ በሚል ስሜት ያናውዘዋል፡፡ በሥነ ፈለክ ዘይቤ ከወር ዐሥራ አምስት የጨረቃ ቀናት የፍቅር ቀናት ናቸው፡፡ ቀሪዎች ዐሥራ አምስት የጨረቃ ቀኖች ደግሞ የራሱ የሆነ ምሥጢር አላቸው፡፡ በሥነ ፈለክ ምርምር በጨረቃ መባቻ የተፈጥሮ ፍቅር ይጸናል፡፡ የእሳት ነበልባል ይተፋል፡፡ ኄርማ ያንን ሳምንት እሳት ሆኖ ይሰነብታል፡፡ በዚህ ሳምንት ቅኔ በጀ አይለውም፡፡ በአእምሮው የሚወጣ





የሚወርደው ትኩስ ፍቅር ብቻ ነው፡፡ ፍቅር እንደ እሳት ይገርፈዋል፡፡ ውስጡ ይወብቃል፡፡ ከሌላው ጊዜ በባሰ መልኩ በጨረቃ መባቻ “ናርዶስ” በትዝታ እየመጣች በፍቅር ታሰቃየዋለች፡፡ ያን ሳምንት ከቆሎ ተማሪዎች ይርቃል፡፡ ለብቻው ወደ ሜዳ ወርዶ የፍቅር ዜማ ያንጎራጉራል፡፡ ዓለማዊ ዜማ በተወገዘበት መንፈሳዊ ዓለም ሆኖ ሙዚቃ ሲያንጎራጉር በመገኘቱ ብዙ ቀን ተገርፏል፡፡ ጅራፉ ግን ጎድቶት አያወቅም፡፡ የጎዳው የፍቅሯ ጅራፍ ነበር፡፡ ጨረቃ ስትበቅል ስትበቅል ለፍቅረኛው ዜማ ከማንጎራጎር ቦዝኖ አያውቅም፡፡ በዜማው ውስጥ ያለው ትዝታዋ ነው፡፡ ሳምንቱን በናፍቆት ይሰንብታል፡፡ የማያውቀው ነገር ሰውነቱን ይወረዋል፡፡ ከሳምንት በኋላ ፍቅረኛውን እየረሳ ቅኔውን እያነሳ ይቀጥላል፡፡

ያ ፍቅር ለዶክተር ኄርማ እውተኛ ፍቅር ይመስለዋል፡፡ ዳሩ ግን እውነተኛ ፍቅር አይደለም፡፡ የተፈጥሮ ግጭት ነው፡፡ የጨረቃ ብቅለት፣ የከዋክብት ልደት ያመጣው ፍቅር መሰል ፍትወት ነበር፡፡ ደግነቱ ዶክተር ኄርማ በጨረቃ በኩል ያን ያኽል እውቀት የለውም፡፡ በሥነ ፍጥረት በኩል ያለው እውቀት ጥሬ ነው፡፡ የጨረቃን መባቻ ለይቶ አያውቅም፡፡ ለፍቅርም ቀን ቀን ያለው አይመስለውም፡፡ የአዳም ዘንግም ቀን ጠብቆ ፍቅር እንደ ሚሰብክ ሊገባው አይችልም፡፡

ቢያውቅ ኑሮማ ፍቅር ወር ጠብቆ ሲመጣ ሰውነቱ እንደጋመ ያውቅ ነበር።

የሆነው ሆኖ በቅኔ ቤቱ አሉ ከተባሉ ዘራፊዎች ቀዳሚው ዶክተር ኄርማ ሆኗል። ተሰባስበው መወድስ ከሚዘርፉ ሊቃውንት መኻል ድምፁም ቅኔውም የሚያምረው የኄርማ ድምፅና ቅኔ ነበር። ወደስዉሩ ዓለም ሲያቀኑ ገምራው ቀጥ ብሎ ቁሞ ከኄርማ አንደበት መወድስ ሲንጎደጎድ ያዳምጥ ጀመር። የቅኔ አጠጣሉ ገምራውን መስጦታል። ታሪኩ ይባስ ብሎ ዐይኖቹን ጨፍኖ እየተደመመ ነበር። ቅኔ ዘርፎ ሲጨርስ ሁለቱ ቁመው ይመካከሩ ጀመር። ወደ ተዋነይ ዓለም ሊጠሩት ነው።

"ዶክተር ኄርማ አብሮን ቢሄድ መልካም ይመስለኛል። የምንሄድበት ዓለም ሁለት ዓለም ነው። ገሀድና ስዉር ክፍል አለው ይባላል። አብሮን ይሂድ። እኛ ከስዋሬው ዓለም ያጠናነውን ምሥጢር እነግረዋለን። ልበኛ ስለሆነ ከገሀዱ ዓለም ቁጭ ብሎ ይመዘግበዋል። ለእሱም ጥናትና ምርምር ይሆነዋል። እኛም በእሱ በኩል የአበውን ጥበብ ወደዓለም እናመጣዋለን። መኻል ሀገር ያሉ ከተሜዎች ይሰሙታል። ለእሱም ይጠቅመው ይሆናል። ምርምር ሊሠራበት ይችላል። በዚያ ላይ እኛ መልአከ ሞትን ገዝተን በተዋነይ ዓለም ከቀረን





ኄርማ ተምሮ ወደፍቅረኛው ይመለሳል። ይዘነው እንሂድ።" አለ ታሪኩ።

"ቅኔ ከተቀኘሁ ወደ ፍቅረኛዬ እመለሳለሁ የሚል ተምኔት እንዳለው አውቃለሁ። ያፈቀረ ሰው ደግሞ እውነተኛ የጥበብ ሰው ሊሆን አይችልም። በሁለት ዓለም መኖር ከባድ ነው። የአብነት ተማሪ ብቻውን የሚኖረው ለዚህ ነው። ፍቅር ልቡስ ሥጋ ሰይጣን ማለት ይመስለኛል። ከተቆራኙ ተቆራኙ ነው። በጠበል ቢሉት አይለቅም። ባሕር ቢጠልቁ አየር ቢወጡ የአየርና የባሕር ጋኔን ሆኖ ይዋረሳል። በሰው ልጆች ባሕርይ ሥግው ሆኖ ይላመዳል። ለዚህ ነው የቆሎ ተማሪ ከፍቅር ርቆ የሚኖረው።" ሲል ታሪኩ ፈገግ አለ። ገምራው ግን ቀጠለ።

"ፍቅርን ደግሞ አውቀዋለሁ። እኔንም ጀማምሮኝ ያውቃል። ሳላውቀው ነው የተለከፍሁት። ባንድ ክፉ ቀን ተለክፌ ነበር። ልከፍቱ ሊጎዳኝ ጫፍ ደርሶ ነበር። ለዲቁናዬ ያለኝ ክብር መክቶ ይዞልኝ ያንን ፍቅር በመጣበት እግሩ ሸኘቸዋለሁ። መቅመሱን ግን እኔም ቀምሸዋለሁ። በሐሳብ ብቻ ያፈቀርሁ ሳምንት በግንባሬ ተደፍቼ አልቅሻለሁ። ደስ የሚለው የእኔ ፍቅር የጨረቃ መባቻን ተከትሎ የመጣ እንጂ በሴት ውበት የተነደፈ ፍቅር አልነበረም። የጸደይን ጨረቃ ተከትሎ መጥቶ

ከጨረቃ ጋር አወዳደረች፡፡ የቁንጅና ውድድር የተጀመረው ያን ቀን ይመስለኛል፡፡ ሴቶች ይችን ዓለም በቁንጅና ሳይሞሏት ጨረቃና ሔዋን በአዳም ዳኝነት የቁንጅና ውድድር አድርገዋል፡፡

በዚያ ላይ አዳም የጨረቃን ውበት እጽፈዋለሁ ሲላት ሔዋን አኮረፈች፡፡ የሴት ኩርፊያ የጀመረው ያን ቀን ምሽት ላይ ነው፡፡ ዛሬ ሴቶች ከሥራ መልስ ምሽት ምሽት የሚያኮርፉት ያ የሔዋን ልማድ በውስጣቸው ተጽፎ ነው፡፡ ባሎቻቸው ውበታቸውን ከጨረቃ ውበት ጋር አነጻጽሮ የናቃቸው እየመሰላቸው ሴቶች ዘወትር ምሽት ምሽት ያኮርፋሉ፡፡ ወንድ ደግሞ ተላላ ነው፡፡ ሚስቱን ሲያባብል ብዕር ሳይጨበጥ ድርሰት ሳይጽፍ ይሞታል፡፡" አለ ገሞራው የመጀመሪያውን ደረሲ እያወደሰ፡፡

ታሪኩ ውስጥ ፈክቶ እንዲቀጠል መስተፋቅር የተቀቡ በሚመስሉ ዐይኖቹ ጠቀሰው፡፡

"እውነቴን! ሔዋን ባኮረፈችበት የፍቅር ምሽት አዳም በገነት ጓሮ ዘወር ዘወር ሲል አምሽቶ ወደ ቤቱ ሲገባ ደከመው፡፡ ያን ቀን በገነት ያየውን ሳይጽፈው አደረ፡፡ በነጋታው ሔዋን ቀድማ ተነሥታ ከገነት ፍራፍሬ ለቃቅማ ቁርስ ሠራች፡፡ እስከ ስድስት ሰዓት ቁርስ ሲቀምሱ አረፈዱ፡፡





ተትር ላይ ትንሽ ተኙ፡፡ ሲነቁ ፀሐይ ከመጨረሻው መስኮት ደርሳ ነበር፡፡ ፀሐይን ሸኝተው ጨረቃን ተቀብለው ሊመለሱ ከቤታቸው ወጡ፡፡ በገነት ዘወር ዘወር ሲሉ አምሽተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ሔዋን ራት አቀረበች፡፡ ከራት በኋላ ደግሞ የጨረቃን ውበት እንዲረሣ ብዕር እንዳያነሣ የረባ ያረባውን ስታወጋው ውድቅት ሌሊት መጣ፡፡ በሁለተኛው ቀን የተመለከተውንም ሳይከትበው እንቅልፍ ጣለው፡፡ ከዚያ በኋላ ከድርሰት ዓለም ተባረረ፡፡ ዝም ብሎ የሴት ባሪያ ኾነ፡፡ ሰው ብቻ፡፡ ሔዋን በፊት ከድርሰት ኋላ ከገነት ነቀለችው፡፡ የሃይማኖት ሊቆች በሔዋን ምክንያት ከገነት እንደ ተባረረ ጽፈዋል፡፡ መባረሩ አንድ ነገር ነው፡፡ በሊቆች ብዕር ያልተከተበው ግን ከድርሰት ዓለም መባረሩ ነበር፡፡ ከተመሥጦ መውጣቱ ከድርሰት ዓለም ገፍትሮታል፡፡ ጠቅለል ሲል በሔዋን ፍቅር ከድርሰት፣ በሔዋን ስሕተት ከገነት ተባሯል፡፡ ከዚያች ቀን ጀምሮ ሴትና ድርሰት ተጣጥመው አያውቁም፡፡ ሚስት ያለው ሰው የተዋጣለት ደራሲ ሆኖ አያውቅም፡፡ ፈላስፋ ግን ሆኖ ያውቃል፡፡ ሶቅራጥስ ነጭናጫ ሚስት በማግባቱ ፈላስፋ ሆነ ሲሉ የሶቅራጥስ ደቀ መዛሙርት ጽፈዋል፡፡ የሆነው ሆኖ አዳም የተባረረው ከገነት ብቻ አልነበረም፡፡ ከድርሰትም ጭምር ነበር፡፡ ያን ጊዜ ድርሰት እንደ ጀመረ ቀጥሎ ቢሆን ኑሮ ከገነት የተቀዳ ግዙፍ



Scanned with CamScanner

መጽሐፍ ለዚች ዓለም በረከት ይሆን ነበር። ያ ቀርቶብናል። ኄርማም የዚህ ባለ ዕዳ ነው። ከፍቅር ውስጥ ከገባ ሰነባብቷል። አብሮን ቢሄድ ከመንገድ ሊመለስ ይችላል።" አለ ገሞራው።

"ለማንኛውም ምሥጢሩን በጆሮው ሹክ እንበላው። ከፈለገ እኛን ይምሰል። ባይሆን የውኃዋን ምሥጢር ትንፍሽ ማለት የለብንም።" አለ ታሪኩ።

"እንደ ፈለግህ በከፊል ሹክ በለው።" አለ ገሞራው።

ታሪኩ ቀስ ብሉ ተጠግቶ

"እንዴት ነህ ኄርማ?" አለ።

"እግዚአብሔር ይመስገን!"

"ወዴት እየሄዳችሁ ነው? በቅኔ ተመርቃችሁ ወደ አቡሻህር ትምህርት ቤት እየሄዳችሁ ነው? በዚህ ሳምንት ደግሞ ቅኔ ቤቱን ሳይለናበቱ ጠፉ እየተባላችሁ ነበር።" አለ ኄርማ ለመንገድ የተሸከሙትን ዝግንትል ተመለከቶ ረጅም መንገድ እንደሚሄዱ ገምቶ።

"አይደለም! ወደ ሌላ ሀገር እየሄድን ነው።" አለ ታሪኩ። "ቅኔ ልታጠብቁ ወደዋሸራ እየሄዳችሁ ነው? አለ ኄርማ።





"ቅኔውን እንደሸንብራ ቆርጥመን በልተነዋል። አሁን እየሄድን ያለነው ተዋነይ መልአከ ሞትን ወደ ገዘተበት ሰዉር ዓለም ነው። ወደዚያው እየሄድን ነው።" ታሪኩ።

ኄርማ በደስታና በድንጋጤ ክው አለ። ስለስዉሩ ዓለም በተደጋጋሚ ሰምቷል። ለመሄድም ፍላጎት ነበረው። ነገር ግን ወደዚያ ለመሄድ ድፍረቱ አልነበረውም። ድፍረትና ተምኔት ልዩ ልዩ ናቸው።

"እኔስ አብሬ ብሄድ አትፈቅዱልኝም እንዴ?" በድንጋጤ እየተርበተበተ ጠየቀ።

"የለም! የለም! ወደስዉሩ ዓለም ብቅ ስትል በእኔ የደረሰ አይደርስባችሁ እያልህ ትጮኻለህ።" አለ ታሪኩ አስወድዶ አስፈቅዶ ለመውሰድ ፈልጎ።

"እንዴት?" አለ ኄርማ ግራ ገብቶት።

"ስዉሩ ዓለም ከገባህ ዐይንህ ጉድ ያያል። ጆሮህ ጉድ ይሰማል። በዚያ ላይ የስውሩ ዓለም ሴቶች የዋዛ አይደሉም። ወንዶችን ልበ ቢስ ያደርጋሉ። በጥበብ ልበ-ቢስ ካደረጉህ በኋላ እንደ ወደል አኽያ በጀርባህ ሸንኩት ይጭኑኻል። ጀርባህ ከተመለጠ ደግሞ አለቀልህ! መቃብርህ የጅብ ሆድ ይሆናል!! "..ሁ..ሁ...ሁ.." መሄድ የለብህም።" አለ ታሪኩ ።

"ታዲያ ተዋነይ እንዴት አሸያ ሳይሆን ቀረ?" አለ ጌርማ።

"ተዋነይማ ቀደም ብሎ ሐሸማል ሆኖ ነዋ! ተዋነይን ከዚህ ክፉ ነገር መንጭቆ ያወጣው ሞትን ገዝቶ ሐሸማል መሆኑ ነው። ለአንተ ግን የተዋነይ እድል ሳይገጥምህ ይችላል። ሐሸማል ለመሆን እንደከርታታ ኮከቦች አያሌ ዓመታት ሊጨርስብህ ይችላል።" አለ ታሪኩ።

"ከርታታ ኮከቦች ደግሞ እነማን ናቸው?" አለ ቀና ብሎ በጎንጅ ሰማይ ሥር ከርታታ ኮከቦችን እየፈለገ።

"ከርታታ ኮከቦች በስዉሩ ዓለም ውስጥ ያሉት ናቸው። ከተዋነይ በኋላ ትልቁ መሳፍርት የሌላቸው ከርታታዎች ተፈጥረዋል። እኒህ ኮከቦች በስዉሩ ዓለም እንጂ በሰማይ የሉም። በሰማይ ያሉ ከርታታ ኮከቦች ወደመሬት ወርደዋል። በል ደኅና ሰንበት ለዘለዓለሙ። ወደ ስዉሩ ዓለም እየሄደን ነው።" አለ ታሪኩ

ጌርማ አኮፋዳውን ነጥቆ ተከተለው።

"ወደ ስዉሩ ዓለም ስትሄዱ እያየሁ ብቀር ነገ አብዳለሁ። እኔም አብሬ መሄድ አለብኝ። በዚያ ላይ የሞት መግቻው ምን እንደሆነ የሚያጠና የምርምር ሥራ ጀምሬአለሁ። የምርምር ሥራዬ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። ቅኔም ለራሴ



የኸል ተቀኝቻለሁ። ሰምና ወርቅ ከገባኝ ሌላው ቢቀር ምንም አይደለም። ከምርምር ሥራዬ ላይ ባተኩር ይበልጥ ለውጥ አመጣለሁ። አብሬ እሄዳለሁ። አብረን እንሄዳለን። አሁንማ ለእኔም ትዝ አለኝ። ተዋነይ ጥበብ ተምሮ ወደ መኻል ሀገር መጣ የሚባለው ከዚሁ ስዉር ዓለም ከሆነ በል ቀስ ብለህ ምራኝ።" አለ ጌርማ እየተከተለ።

"በእርግጥ እኛም በትክክል አውቀነው አይደለም። ስሙን ግን ሰምተናል። ከተዋነይ ዓለም መግባት ባንችል እንኳን ጥበብ ተምረን እንመለሳለን ብለን መንገድ ጀምረናል። ከእኛ ጋር ለመሄድ ከፈቀድህ ፈረሱ ይኸውና! ሜዳው ግን ሩቅ ነው።" አለ ታሪኩ መንገዱን በጣቱ እያመለከተ።

"ግድ የለም። እግራችን እንዳደረሰን መሄድ አለብን።" ተያይዘው ከቅኔ ቤቱ ወጡ። ጌርማ ዙሪያው ጨልሞበት እንጂ ድሮውንም የተዋነይን ዓለም ለማጥናት ተምኔት ቢኖረው። አሁን ገና መንገዱ ተገለጠለት። እንደ እነሱ ከታብር ሳይቋደስ ተከተላቸው። መንገዱ ወዴት ያደርሰው ይሆን? አንተ አብጀው! የተዋነይ ፈጣሪ ሆይ ወዴት አለህ? የዶከተሩን መንገድ አንተ አብጀው! እኔ አላውቅበትም! የተዋነይ ዓለም ሆይ! ጌርማ እየመጣ ነው!..።

## ፱

### የድንጋይ ናዳ

ጠቢቡ ሖረ ከስዉሩ ዓለም ክፍል ገሀዱን ለመጠበቅ ሲሾሙ ደስተኛ ነበሩ፡፡ በደመና ተጭነው ወደ ስዉሩ ዓለም ገብተው በዚያ ላይ በታማኝነት ጠባቂ ሲሾሙ ራሳቸውን እንደገነት ጠባቂ መልአክ ቆጠሩት፡፡ ከስውሩ ደቅ እስጢፋ እስከ ገሀዷ ደቅ ማርያም በእግር የስድስት ሰዓት መንገድ ነው፡፡ በእግራቸው ሲርቃቸው እንደተዋነይ በደመና እየተወነጨፉ ይጠብቁ ጀመር፡፡ በል ሲላቸው ደግሞ ደቅ ገዳም ገብተው ከአረኛዎች ጋር ሲያወጉ ይውላሉ፡፡ እሁድና ቅዳሜ ሰዓታት ይቆማሉ፡፡ ከዐባይ ዳር ወደደቅ እስጢፋ የሚወርዱ ዘላኖችን ሲመለከቱ እንደለመዱት በደመና ተንሣፈው የድንጋይ ናዳ ያወርዱባቸዋል፡፡ ዘላኖች ነፍሴ አውጭኝ ብለው ከብታቸውን እየነዱ ወደመጡበት ይመለሳሉ፡፡ እንዲህ እያደረጉ ከደቅ ማርያም እስከደቅ እስጢፋ ያለውን ገሀዱን ሀገር በደንብ እየጠበቁ ነው፡፡ የስዉሩን ዓለም ጫካ የዘላኖች እግር ሳይረግጠው ለነበተ፡፡





## ፲

### ፍኖተ-ጃንሆይ

ኮርታታ ኮከቦች ጉዞውን ቀደም ብለው ጀመሩት፡፡ የንጋት ኮከቦች በዳንግላ ሰማይ ሥር አልፈው አልፈው ቦግ ቦግ ሲሉ ከተዋነይ ሀገር ተነሥተው መኻል ጎጃምን ሰንጥቀው ዳንግላ ደረሱ፡፡ ለገሞራው ጃንሆይ ትዝ አሉት፡፡ እናም አዲስ ወግ መዘዘ፡፡

"ይህ መንገድ ጃንሆይ መንገድ ይባላል፡፡ ከዳንግላ ተነሥቶ ጃዊ ይገባል፡፡ በሰዎች ዘንድ የጃንሆይ መንገድ ውስብስብ ትርጉም አለው፡፡ ከፊሉ ጃንሆይ ከስደት መልስ በዚህ በኩል አድርገው ወደ ቤተ መንግሥት መመለሳቸውን ይተርካል፡፡ ስያሜውም ከዚህ ጋር ይየያዛል ይላል፡፡ የተዋነይ የጥበብ ልጆች ግን በዚህ አይስማሙም፡፡ መንገዱ ጃንሆይ ወደ ደቅ እስጢፋ የሄዱበት መንገድ ነው ሲሉ ይተርካሉ፡፡ የሞት መድኃኒት ጎሥሣ የወጡ ሰሞን ወደ ደቅ የሄዱት በዚህ በኩል ይመስለኛል?፡፡" አለ ገሞራው ጌርማ የጥናት ማኅደሩን ገልጦ ፍኖተ ጃንሆይ ሲል በማስተምሻው ከተበ፡፡

"ደቅ ለመሄድ ዳንግላ ድረስ ምን አመጣቸው? መንገዱ ያለው በእንጀባራ አድርጎ ቻግኒን ተራምዶ ቀጥታ ነው፡፡



Scanned with CamScanner

ዳንግላ ድረስ ምን አመጣቸው?፡፡" አለ ታሪኩ፡፡ ኄርማ ታሪኩ የተናገራትን ቃል በቃል ከተበ፡፡

"በጊዜው ወደ ደቂቀ ተዋነይ ለመሄድ አርጌ ዳንግላን መሳለም ያስፈልግ ነበር፡፡" አለ ገሞራው ፈገግ እያለ፡፡

"ለምን አስፈለገ? አሮጌው ዳንግላ ውስጥ ከደቂ ጋር የተያያዘ ምን ምሥጢር ነበር?" አለ ኄርማ ለመከተብ እየተቻኮለ፡፡

"እሱን ከአሮጌው ገበያ ስንደርስ ጠይቀኝ፡፡ መንገድ መሪው እኔ ነኝ፡፡" ብሎ ወደ አሮጌው ዳንግላ ይዟቸው ተቀለበሰ፡፡ ከመኪናው መንገድ ወደ ገጠር ገባ ብሎ ወዳለው መንገድ ሲዘልቁ እያወጉ ነበር፡፡

ከአሮጌው ዳንግላ ሲደርሱ "ይህ ገበያ ድሮ የስዉሩ ዓለም ጠቢባን ገበያ ነበር፡፡ ተዋነይ ሴት ተከትሎ ወደ ስዉሩ ዓለም ገባ የሚባለው ከዚች ገበያ ተነሥቶ ይመስለኛል፡፡" ገሞራው ከገበያ መኻል ቆሞ መተረክ ጀመረ፡፡

"እንዴት አወቅህ?" አለ ኄርማ፡፡





"አውቃለሁ! በከፊል አውቃለሁ! ታች አምና የተዋነይን ታሪክ ለማጥናት ተፍ ተፍ እያልሁ መጥቼ ነበር፡፡ አንድ ወጣት እየመራ አመጣኝ፡፡

ያን ቀን የመከረኝም ትዝ ይለኛል፡፡ የቆሎ ተማሪ ነኝ ብለህ ሕይወትህን እንዳታጣ፡፡ አደራ! የዚህ አካባቢ ሰዎች ሲጠይቁህ ከአስኳላ ትምህርት ቤት የመጣሁ የታሪክ ተማሪ ነኝ በላቸው፡፡ እኔም ከእናቴ ሀገር ከዘጌ የመጣ አስኳላ ተማሪ ነው እላለሁ የሚል ምክር ሰጠኝ፡፡ ለመንደሩ ሰዎች ቃል በቃል ይህንን ነገርኳቸው፡፡ እነሱም ምሥጢራቸውን ዘከዘኩልኝ፡፡ ስለደቂቀ-ተዋነይ ለማንሣት ግን ድፍረቱ አልነበረኝም፡፡ ቀጥቅጠው ይጥሉኛል ብዬ ትንፍሽ ሳልል ቀረሁ፡፡" አለ ገሞራው ታች አምና በተዋነይ ዙሪያ የሚያጠነጥን ታሪክ ሲያጠና ከቃረመው ተነሥቶ፡፡

"የዚህ መንደር ሰዎች ከደቂቀ ተዋነይ ጋር ተዛምዶ አላቸው እያልህ ነው?" አለ ታሪኩ፡፡

"በጥናቱ አልደረስሁበትም፡፡ ቅድመ አያቶቻቸው በእንደበታቸው ከትግራይና አገው እንደመጡ ይናገራሉ የመንደሩ ሰዎች፡፡ ሀገሩም ኳኩራ ይባላል፡፡ ኳኩራ የአገው እምብርት ነው፡፡ ኳኩራ ማለት የተለያየ ትርጉም ቢኖረውም እኔ ግን ፀሐይ በሚለው እስማማለሁ፡፡ ኳራ ማለት በአገውኛ

ፀሐይ ማለት ነው። በቋረኛ ደግሞ ቋራ ማለት ፀሐይ ማለት ነው። ኪኩራና ቋራ ተመሳሳይ ቃላት ናቸው።" ካለ በኋላ ወደ ደቅ ሴቶች ታሪክ ተራመደ።

"ድሮ የስዉሩ ዓለም ሴቶች ከዚህ ገበያ እየመጡ ሎጋ ሎጋውን ኮበሌ እየመለመሉ መውሰድ ሲጀምሩ ያ ክፉ ወሬ ተወራባቸው። ከዚያ በኋላ ሴቶች ወደ ዚህ ገበያ መምጣት አቆሙ።" አለ ገሞራው አብሮ የነበረ ይመስል።

"ምን ወሬ ተወራባቸው?" አለ ጌርማ።

"አንተ ለቅኔ ቤት አፈ ታሪክ እንግዳ ስለሆንህ ላትሰማው ትችላለህ። ቆይማ በደንብ ላስረዳህ። ዶክተር የሚለውን ዘመናዊ መዓርግ ተጠቅመህ ታሪኩን ለሀገሬ ልጆች ታደርሰዋለህ። እኔ የቆሎ ተማሪ ስለሆንሁ ብለፈልፍ የሚሰማኝ ሰው የለም። ያሁኑ ትውልድ በስምና በወረቀት እንጂ በእውቀት አያምንም። ውትልፍ ብቻ!።" ብሎ በረጅሙ ይግተው ጀመር።

"ይኸውና ጌርማ እኛ ኢትዮጵያውያን ከዐድዋው ጀግንነት እኩል ለወሬም ኃያላን ነን። በድኅነትና ስም በማጥፋት የሚደርስብን የለም። እናልህ የስዉሩ ዓለም ሴቶች ከዚህ ገበያ ጠፍተው አያውቁም ነበር። ሴቶች ወደዚህ ገበያ





እየመጡ ኮበሌ እየመረጡ ለባልነት ይወስዱ ነበር። ሲወስዱ ደግሞ መሰውር ይጠቀሙ ነበር። መሰውሩ የሚመጣው ከደቅ እስጢፋ ነው። ከስዉሩ ዓለም። ይህንን ማንም ባላገር ይተርከዋል። የስዉሩ ዓለም ቆነጃጅት ሸበላ ሸበላውን እየመረጡ ሲወስዱ የእኔ ቢጤው ድንክ ቀመስ እየተመረጠ ቀረ። በዚህ ጊዜ በዚህ አካባቢ ጆሮ ጭው የሚያደርግ ወሬ ተናፈሰ።"

"ምን ተብሎ ተወራ?" አለ ጌርማ ሲከትብ ብዕሩን እያስተካከለ። "ማንም እየተነሣ እንጎቻ በቀደደው አፉ የደቅ ሴቶች የሰውን ልጅ ወደ አኽያ የሚለውጥ ጥበብ አላቸው። ሰውን በሬ አድርገው ያርሳሉ። በግ አድርገው ይሸጣሉ። እነሱም ትኋን እየሆኑ ይናከሳሉ። ሊማሊሞን ፎገራ፣ ፎገራን ሊማሊሞ አድርገው መልክአ ምድር ሳይቀር የመለወጥ ኃይል ከሰይጣን ተሰጥቷቸዋል እያለ ወሬውን ይቀደው ጀመር። በዚህ የጥላቻ ስብከት ካህናት ሳይቀር ተባበሩ። ከዚህ አንጉል ስብከት በፊት ሴቶች በአሮጌው ዳንግላና በጫራ ደቅ ገበያ አይጠፉም ነበር። ደቅ ጫራ ከእሱ አዲስ ቅዳም ዝቅ ብሎ ያለው ገበያ ነው። በኋላ ግን ሰው እያወቃቸው ጥላቻው እየጠናባቸው ሲሄድ በገሀድ ገበያ መዋሉን አቆሙ። ከዓመት ወይም ከሁለት ዓመት አንድ ጊዜ መኻል ሀገር ሲናፍቃቸው ወደአሮጌው ዳንግላም ሆነ ወደጫራ ገበያ ሲመጡ ነጋዴው



Scanned with CamScanner

ገሞራው የሀሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ሳለ ጀምሮ የቅኔ ዘራፊ ነው:: ከዚያ ጀምሮ የሰማውን ታሪክ ከዘከዘከላቸው በኋላ ጌርማ በተባ ብዕሩ ከተበው:: ከዚያም መልሶ ሲያነበው በፍሥሓ ተዋጠ:: ገሞራው ግን ፋታ ወስዶ ወደ ባሪያ ንግዱ ታሪክ አለፈ::

"ዘዚህ በዳንግላ ገበያ ሌላም አስታያሚ ታሪክ ተፈጽሞበታል:: ከጊዜ በኋላ ገልቱ ነገሥታት ገበያውን የባሪያ ንግድ ማዕከል አድርገውት ነበር:: በዚህ ስፍራ እንደልባቸው ባሪያ ቸብችበውበታል:: ደራሲው አዲስ ዓለማየሁ በዚህ ስፍራ ሳሉ የባሪያ ንግድን ለመግታት ከባሪያ ፈንጋዮች ጋር ተፋልመዋል:: ከዘማቹና ከባለቅኔው ጤናው ዘዳንግላ ጋር ወዳጅነት የመሠረቱትም ከዚህ ስፍራ ላይ ነበር:: ጤናው መጀመሪያ ታዋቂ ሽፍታ ነበር:: አቶ ሐዲስ የባሪያ ንግዱን ለመግታት ሲራወጹ እንዲያግዛቸው ጥሪ አቀረቡለት:: ወድዶ ገባ:: ኋላ በጣሊያን ወረራ ጊዜ እስኪዘምት ረዳቸው:: በጣሊያን ወረራ ጊዜ ለሀገር ተሰዋ::" ዘወር ዘወር እያሉ ገበያውን እየቃኙ ሳለ ገሞራው ቀጠለ::

"አሁን ገበያው ነጻ ወጥቷል:: እንደምታዩት ከስሙ በቀር ገጽታው ያን ዘመነ መከራ የሚያመለክት የታሪክ ቅሪት የለውም:: በመልካም ሁኔታ ላይ ይገኛል:: የባሪያ ፍንገላውም





በሥልጣኔ ተገርስሷል:: አበስኩ ገበርኩ:: ይህንን የሠሩ ገልቱዎችን ፈጣሪ ይቅር ይበላቸው::" ብሎ መንገዱን ቀጠለ:: ወደማታ አገው ምድር ገቡ:: ከኮሶ በር በፊት የመሸታ ጣሳ የወረራት ከተማ አገኙ:: እንጅባራ ትባላለች::

እንጅባራ አየሯ ቀዝቃዛ ነው:: ዙሪያዋን የኮሶ ዛፍ ከቧታል:: የመሸታ ቤቶች ይበዛሉ:: ገሞራው ዘሎ ወደአንድ ትኩስ መሸታ ቤት ተቀላቀለ:: ስለስዉሩ ዓለም የሚለቃቅመው ትኩስ ወሬ ፈልጎ ነው:: ጉዟቸው ወደ ስዉሩ ዓለም ስለሆነ በዚህ አካባቢ ከአዛውንቶች የሚነዛውን የስዉሩን ዓለም ታሪክ እንደምርኩዝ ይጠቀሙታል:: ወደ መሸታ ቤት ሊገባ የቻለው በስዉሩ ዓለም በኩል የወዳደቀ መረጃ ፍለጋ ነበር:: ወደስዉሩ ዓለም ሲቀለበሱ ኮሶ በር ሲደርሱ ምንም አልቀራቸውም:: ስዉሩ ዓለም በሀገራችን ምዕራባዊ ጫፍ የሚገኝ ሲሆን ከአዲሳባ ተነሥቶ ወደ ባሕር ዳር ሲሄዱ ኮሶበር ለመድረስ በእግር አይታሰብም:: በመኪና ግን የስምንት ሰዓት መንገድ ነው:: ከባሕር ዳር ኮሶ በር በእግር ያንድ ቀን ተኩል መንገድ ነው:: ለከተማዋ የአገው ምድር የፈረስ ጉግስ መገለጫዋ ነው:: ገሞራው ቅኔ ቤት ሳለ ቀርቅሃና የፈረስ ጭራ ኮሶ በር እየገዛ ባሕር ዳር እየወሰደ ይነግድ ነበር:: በሌላ በኩል ደግሞ የፈረስ ማኅበር የሚባል በዓመት አንድ ጊዜ ፈረሰኞች

# ፲፩

## ስዉሩ ሰው በደቅ

ዐራት ዐይናው ደጎና ጥበቃ ሆነዋል:: ስዉሩን ዓለም ሲጠብቁ ቀኑ ቶሎ እንዲመሽላቸው አቡሻህር መጽሐፋቸውን ሹጉጠው ልሙጡ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለዋል:: ከዚያም አንዲት ቀመር መዝዘው ከመጽሐፉ ያወጣሉ:: ያን ብሉየ መዋዕል የሆነ ቀመር እስኪቀመሩ ጀንበር ወደመስኮቷ ትቃረባለች:: በቃላቸው ቀምረው በሦስት ባራት መንገድ እስኪያረጋግጡ ድረስ ጀንበር የለችም:: አቁማቸው አድማሳትን አልፋ ትጠልቃለች::

አሁንም አንድ ቀመር መዝዘው እየቀመሩ ነበር:: አቀማመጣቸው ደግሞ የጉድ ነው:: ዘወትር ከሚሰየሙባት ድንጋይ ላይ ወደል ከምር አክለው ተጎምረዋል:: አቤት ግርማ ሞገስ! አቤት ሊቅነት! አቤት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ! እንኳን ተናግረው ዝም ብለው ያስፈራሉ:: የሰብእናቸው የደስ ደስ የሚታወቀው ሲቀርቧቸው ብቻ ነው:: አሁንም መጽሐፋቸውን ዘርግተው የሞት ቀናቸውን ገሰጡ:: በዘንድሮው ፍካሬ ዘመን መሠረት ዕለተ እረፍታቸው ደርሶ





ነበር:: ከኅብስተ መናው ተቋድሰው መልአከ ሞትን ወደኋላ ገፈተሩት::

የሞትን ቀጠሮ ሠርዘው ይችንን ዓለም በድጋሚ በፍሥሐ ተቀበሏት:: አዲስ ሥጋ ለብሰዋል:: አዲስ ዓለም ጀምረዋል:: በዘንድሮው ፍካሬ ዘመን ሞት እንደ ሌለባቸው ከሞት ጋር ተፈጣጥመዋል:: ሐሽማል ሆነው ስዉሩን ዓለም እየጠበቁ ነው:: ስዉሩ መልአክ ቀለሙ ዘቦሩ ሜዳ ሥላሴ ማንም ውትልፍ ወደ ስዉሩ ዓለም ገብቶ ጥበብ ጨልፎ እንዲወጣ የፈቀዱ አይመስልም:: አጥብቀው እየጠበቁ ነው:: ተሰውሮ ስዉር ዓለም የሚጠብቅ ስዉር መልአክ ኾነዋል::



Scanned with CamScanner

# ፲፪

## ምድረ ሞርካ

ዶክተር ኄርማ የደራሲ ብዕሩን እየኮለኮለ ነው:: ገሞራውና ታሪኩ ከመንገዳቸው ጎን ለጎን ጠለቅ ጠለቅ ያለ ሐሳብ እያነሡ ሺናሻ ደረሱ:: መንገዱ ሰላማዊ መንገድ ነበር:: ገሞራው ቀደም ባለው ዘመን ሺናሻን በተደጋጋሚ ረግጠዋታል:: ከቅኔ ቤት ሳለ ወደ ሽናሻ ዘወር ዘወር ብሎ ከጥበባቸው ለመቋደስ ደክሟል:: ሽናሻ ሲደርሱ የሞርካና የጃንሆይ ታሪክ ትዝ አለው:: ትልቁ ሰው ሞርካ በጃንሆይ ዘመን በሽናሻ ጌታ ነበሩ:: ሞርካ ከሚባል ጎሳ የተገኙ ሲሆኑ ሞርካ እንደነቢይ ይቆጠሩ ነበር:: በሽናሻዎች ዘንድ ነቢዩ የሚል ቅጽል ስም አላቸው:: በጃንሆይ ዘመን ተራው መኳንንት ይቅርና ራሳቸው ጃንሆይ ይፈሯቸው እንደ ነበር ያልተጻፈ፣ ነገር ግን አንድ እውነታ አለ:: ገሞራው ያንን ታሪክ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: የሽናሻን ምድር ሲረግጡ ሞርካን አስታውሶ ወግ መዘዘ::

“ወደ ስዉሩ ዓለም በተስፋ እንድመጣ ያደረገኝ የተዋነይ ታሪክ ብቻ አይደለም:: የሞርካ ታሪክም ወደ ስዉሩ ዓለም





ለመሄድ ቀስቅሶኛል::” አለ ሦስቱ ተጓዦች የሞርካን ምድር ሊረግጡ::

“ሞርካ ደግሞ ማን ነው?” አለ ኄርማ የሞርካ ምድር ሲል ከማስታዎሻው ላይ ከከተበ በኋላ ብዕሩን በቀጫጫ ጣቶቹ እየኮለኮለ:: ዋንጫ ቢጤ ጥፍሮቹ እንሶስላ የሞቁ ይመስል ያብረቀርቃሉ::

“ሞርካ በጃንሆይ ዘመን የሽናሻ ገዥ ነበሩ:: ጃንሆይ ግን ሹመቱን የሰጧቸው በሰምና ወርቅ መንገድ ነው ይባላል:: ሰሙ ላይ ከላይ ሞርካ በሽናሻዎች ዘንድ ብቁ መሪ ነበሩ:: ወርቁ ሲፈለቀቅ ግን በስዋሬ በኩል አንቱ የተባሉ ጠቢብ ናቸው:: ጃንሆይ ሞርካን አጥብቀው ይሰጓቸው ነበር ይባላል:: ስጋታቸው ደግሞ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ከዙፋኔ ይፈነቅሉኛል ብለው አይደለም:: በመሰውሩ ነው::” አለ ገሞራው:: የዘውዱ መንግሥት አማካሪ የነበረ ይመስል::

“ሞርካ ይሰወሩ ነበር?” አለ ታሪኩ::

“ምንም ጥርጥር የለውም:: ይሰወሩ ነበር:: ጃንሆይም በተለያዩ ጊዜያት በዚህ በኩል ፈተና ደርሶባቸዋል ስለዚህ የጥበብ ሊቆችን ይፈራሉ:: ጃንሆይ ራሳቸውም በጥበብ ያምናሉ:: አልፎ አልፎም በማእምርነት ይጠራጠራሉ:: ከዚህ

የተነሣ የጥበብ ሰዎች በውስጥ ፈርተው ከላይ ከላይ አክብረው ይኖሩ ነበር። ከእኒህ ክቡራን ውስጥ ምር[illegible] አሉበት። በጥበባቸው ይፈሩ ነበር።" አለ ገሞራው

ጌርማ በአሉታ አንገቱን ነቅንቆ

"ይህ ወሬ የጃንሆይን ሰብእና ዝቅ የሚያደርግ ወሬ ነው። ከታሪክ አንጻርም ኋላ ቀር ታሪክ ይመስለኛል። ስም ማጥፋት ካልሆነ በቀር ጃንሆይ በምርካ ጥበብ የሚሸበሩ ተራ ሰው አልነበሩም። ከጃንሆይ ይልቅ መኳንንቱ ጠቢባንን ይፈሩ ነበር። በዚያ ላይ የምርካ ስምና ታሪክ በዚህ መሰል ትርክት አልተጻፈም። በጊዜው የነበሩ የሀገረ-ገዥዎች ስም ከሞላ ጎደል በየታሪኩ ተጽፏል። የዘውዱ መንግሥት አማካሪና የአውራጃ ገዥዎች ስም ከሞላ ጎደል በታሪክ ተካቷል። ከምትለው ውስጥ ምርካ የሚባል የሺናሻ ገዢ አልተጣፈም። የጉምዝ ምድር ምርካ በሚባል የጎሣ መሪ እንደተገዛም አሁን ድረስ ተጽፎ አንብቤ አላውቅም።" አለ ጌርማ

"እኔም የተጻፈ ታሪክ መልሶ መተረክ አልወድም። ጥብቅናዬም በታሪክ ለታወቁ በታሪክ ለደመቁ አይደለም። ለከርታቶች ነው። ከርታታ ኮከቦችን እየፈለጉ ማውሳት ነው ሥራዬ። ካልፈለግህ ዝም በል። ለታሪኩ ሳውጋው። ከፈለግህ ደግሞ የምርካ ምድር በጃንሆይ ዘመን የሚል ርእስ ጀምር።





አስደናቂ ጥናት ይወጣዋል። ለሕዝብ ጆሮ ታደርሰዋለህ። እኔም ምርካን ያነሣሁት በዘፈቀደ አይደለም። ከስዉሩ ዓለም ጋር አያይዤ ነው። እኛም ወደዚህ እንድትመጣ የመረጥንህ የስዉሩን ዓለም ምሥጢር ጽፈህ ለሕዝብ ጆሮ ታደርሰዋለህ ብለን ነው። አሁን ባለው ትኩስ ትውልድ የምትቀርበው አንተ ነህ። እኛ በእድሜ ሳይሆን በአማርኛ ተራርቀናል። ይች ቅኔ ቤት አሁን ካለው ትውልድ አርቃ ቀብራናለች። ዶክተር የሚል ቅጽል ስለ ሌለን ብንናገር የሚሰማን የለም። ስም ያስፈልጋል። ዘመኑ የስም እንጂ የእውቀት ዘመን አይደለም። ይህ ልብልብ ዘመን የወረቀት እንጂ የክሒሎት ዘመን እስኪሆን ማዕረግ ያለው ሰው ያስፈልገናል። እንደ አሮን አፍ ትሆነን ዘንድ መርጠንኻል። እኛ ከቅኔ ቤት ከቀሰምነው ተነሥተን የአበውን ምሥጢር እንደከህሎትህ እናስረዳኻለን። አንተ ዶክተር የሚለውን ዘመናዊ መዓርግ ተጠቅመህ ወደ ሕዝብ ጆሮ ታደርሰዋለህ። አንተ ግን ገና ከወዲሁ ተቃውሞ አታብዛ። በዚህ ሁኔታ የስዉሩን ዓለም ምሥጢር እንደ ወረደ ትጽፈው አይመስለኝም። የብዕር ሰው እንደ ወረደ ካልጻፈ ብዕረኛ ሊባል አይችልም። ተራው ሰው እንደ ፍጥርጥሩ የወደደውን መርጦ ሊሰማ ይችላል። ብዕረኛ ግን የወደደውን ብቻ መርጦ መመዝገብ የለበትም። እሱ የወደደውን ብቻ የሚከትብ ከሆነ ብዕሩ አድሳዊት ናት።

“እሱን እንኳን በዚህ በኩል እንጠረጥረውም:: መውጫ ያለፈ የአዳም ዘንግ ያለው አይመስለኝም::” አለ ከሽንት ታሪኩ ለገሞራው አግዞ

“ምን ይታወቃል:: ለፍቅር ቀመር የለውም:: ባንድ ሌሊት ጭምቱን እብድ ያደርገዋል:: እኔም የመንደሩ ጭምት ነበርሁ:: ፍቅር ሲያሳብደኝ ደረስሁበት::” ካለ በኋላ

“ይቅርታ ገሞራው! የሞርካን ጥበብ በደንብ አምጣው:: እንደወረደ እጽፈዋለሁ:: ወደከተማ ስመለስ እንደወረደ በራድዮ እተርከዋለሁ:: ዓለም የሞርካን ስም እያነሣ ለጥበብ እንዲዘምር አድርጋለሁ::” አለ ጌርማ ብዕሩን ከወረቀት ጋር እያናከሰ::

ገሞራው ቀጠለ

“ታሪኩን የነገሩኝ የፊደል መምህሬ ናቸው:: ከስዉሩ ዓለም ሲገቡ ወደዚህ ምድር ብቅ ባሉበት ዘመን ከሞርካ ጋር ቆይታ ነበራቸው:: ቆይታቸውም ይህን ይመስላል::” ብሎ የሞርካንና የመምህሩን የቆይታ ታሪክ መተረክ ቀጠለ::

“ሞርካ በጥበብ በኩል አንቱ የተባለ ሰው ሲሆን በአጀብ የሚኖር ጌታ ነበር:: ጌታ ያደረገው ደግሞ ከስውሩ ዓለም የወረሰው ጥበብ ነው ይባላል:: በእርግጥ የሸናሻ ሰዎች





በባሕላዊ መድኃኒት የታወቁ ናቸው:: አንዳንዶች ግን ከባዕድ አምላኮ ጋር ጭምር ያያይዙታል:: በግሌ ያ ባይሆን መልካም ነበር እላለሁ:: ዳሩ ግን ሞርካም ለአያሌ ዓመታት የሸናሻን ምድር ፈንጭቶባታል:: ከጥበቡ ለመቃመስ የደጋው የቆላው ሕዝብ ውሎ አዳሩ ከዚሁ ሽናሻ ነበር:: ከጃንሆይ ጀምሮ ደጁን ያልረገጠ መኳንንት አይገኝም ነበር ይባላል:: በተለይ የቅኔ ተማሪዎች ቁጥር አያሌ ነበር:: በጊዜው መወድስ እምቢ ያላቸው ውሽልክ ውሽልክ ተማሪዎች የሞርካ አገልጋይ ነበሩ አሉ:: ለትምህርት ብለው ከሀገራቸው ከወጡ በኋላ ወደ ዚህ ምድር መጥተው ለጥበብ ደጅ ያልጠኑ የቅኔ ተማሪዎች አይገኙም:: ከእኒህ መካከል የእኔ መምህር ቀዳሚ ነበሩ:: የእሳቸውን ልዩ የሚያደርገው ግን ቅኔ ከዘረፉ በኋላ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደሞርካ ብቅ ማለታቸው ነበር:: በቅኔ ሊቅ ቢሆኑም ቅሉ ወደ ሞርካ መጥተው ደጅ መጥናታቸውን ግን አውርተውኛል:: እሱን ነው እያወጋኋችሁ ያለሁት:: እንዲህ ነበር የሆነው::” ብሎ ስለደ ከመው ጥቂት አረፍ አለ:: ፀሐይ ከምዕራባዊ መስኮቷ ለመወሸቅ እየተቃረበች ነው:: ኬክሮሷ መንምኗል:: አድማስ ቀርቧታል:: ናጌብ ርቋታል:: ገሞራው ፀሐይን ሲመለከት የፀሐይ ቀመር ጭልጥ አድርጎ ወሰደው:: ድሮ ቅኔ ቤት ሳለ ቀን ከደሳሳ ጎጆው ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ሲጽፍ ይውላል::



Scanned with CamScanner

አሁንም ዐይኖቹን ከምሽቷ ፀሐይ መቀነት ላይ ወረወረ። ፀሐይ እየቀዘቀዘች የጸደይ ጨረቃ እየደመቀች ነበር። ቀዝቃዛው አየር የሞርካን ምድር መቀደስ ጀምሯል። ኄርማ ሲከትብ ገሞራው ቀጠለ። ታሪኩ በራሱ መንገድ እየተመሰጠ ነበር። የጎንደር ታሪክ ትዝ ብሎት ይሆናል።

"የሞርካ ስዋሬ ከስዉሩ ዓለም ጥበብ ጋር ይየያዝ ይመስለኛል። ስዋሬአቸው የተዋነይን ስዋሬ ይመስላል።" ብሎ ዝም አለ። ኄርማ ወጉን እንደወረደ ከትቦ ሲጨርስ አሁንም በስሱ ተቃወመ።

"ሐሳቡን እንደወረደ ከትቤዋለሁ። የዕፀ መሰውሯ ነገር ግራ አጋቢ ነው። በተለይ የጃንሆይን ወደሞርካ መምጣት ከጥናቴ ውስጥ ከትቼ በራድዮ የምተርከው አይመስለኝም።" አለ ዶክተሩ።

"ለምን ይህን የመሰለ ወግ ከሕዝብ ጆሮ አላደርሰውም ትላለህ?" አለው ገሞራው ኄርማን።

"የፊደል መምህርህ ወደ ሞርካ መጥተው ሊሆን ይችላል። የጃንሆይ ከሞርካ ቤት መምጣት ግን በዜና አውታሮች አልሰፈረም። በፍሬ ከናፍርም ሆነ በጃንሆይ የታሪክ መጽሐፍ የሰፈረ አይመስለኝም፥ ጃንሆይ ወደዚህ ምድር በተደጋጋሚ





መምጣታቸው አቴጌ መነንም በዚህ መንደር ለሚኖሩ የእኽል ወፍጮ ማበርከታቸው ተነግሯል። አሁንም ባላገሩ ይተርከዋል። ወደ ሞርካ መምጣታቸው ግን በታሪክ ማኅደር አልሰፈረም። በዚያ ላይ ጃንሆይን ዝቅ ዝቅ እያደረጉ መናገር አግባብ አይደለም። ለጥናትና ለምርምሬም ዋቢ ሊሆን አይችልም። በረኃ ለበረኃ የምንከራተተው በትክክል ስዉሩን ዓለም ገልጣችሁ ታሳዩናላችሁ ብዬ ነው። ይህን የመሰለ ዝቃጭ ወሬ ከጠጅ ቤትም ቢሆን አላጣውም። ካልፈለጋችሁ ወደአዲሳባ ተመልሼ ጠጅ ቤቶችን እቀላቀላለሁ። ጠጅ ቤት ከሚዘባርቁ ወፈፌዎች ከዚህ የተሻለ ወግ ተርፏል።" አለ ኄርማ የምርም የቀልድም ንግግር።

"ጠጅ በት የሞርካ ታሪክ የለም። አሁን አሁን ጠጅ ቤት ይቅርና ቅኔ ቤት እንኳን እየቀረ ነው። እርግጥ ነው ድሮ ጠጅ ቤት ሊቆችም የወጉን ያደርሱ ነበር። እንዲያውም ድሮ ከሊቆች አንዳንዶች የቤተመንግሥት ወሬ ሲፈልጉ ጠጅ ቤት ብቅ ይሉ ነበር አሉ። በተለይ ዐራቱን ጉባኤያት የሚያውቁ ከጎንደር አለቃ አየለ የሚባሉ ዐራት ዐይና ሊቅ ነበሩ። በጃንሆይ ዘመን ፊት አዲሳባ፣ ኋላ ጎንደር ላይ ያስተምሩ ነበር። ከቤተ መንግሥትም ዐራት መቶ ብር ደመወዝ ይሰጣቸው ነበር። ዐራት ዐይናው ግን ከዚች ከዐራት መቶዋ ሁለቱን መቶ ከፋፍለው ሐምሳ ሐምሳዋን ለብስል ለብስል



Scanned with CamScanner

ተማሪዎቻቸው ያነፍሷቸው ነበር አሉ። ፍቅረ ንዋይ ጨርሰ ከጠፉላቸው ሊቆች ቀዳሚው እኒህ ሊቅ ነበሩ። ከእኒህ ዐይናማ ሊቅ በቀለም የተወለዱ አንዳንድ ሊቆች ጠጅ ቤት እየሄዱ ከመኳንንቱ ጋር ሲቀላለዱ ያመሹ ነበር። መሄዳቸው ጠጅ ፈልገው አይደለም። በድሮው ጊዜ የቤተ መንግሥቱ ምሥጢር በከፊል የሚወጣው በጋዜጣ አልነበረም። በጠጅ ቤት በኩል ነበር። ሊቆችም ከወሬውም ከጠጁም ለመቀማመስ ጠጅ ቤት ብቅ ይሉ ነበር። አሁን ግን ጠጅ ቤት በራሱ ቀርቷል። ጠጁ ቀርቶ ቅራሪም የለም። እረ የጠላ ቅራሪም ነጥፏል። ዐራት ኪሎ ደርቃለች። ድሮ ዐራት ኪሎ ዙሪያ የነበሩ ጠላ ቤቶች ጠጅ ለምኔ ነበሩ። አሁን ግን የለም። እንዲያውም ድሮ ድሮ

ዐርብ ልብስ እጠቡ፣ ቅዳሜ ተኩሱ።

እሁድ ዐራት ኪሎ፣ ጠበል እንድትቀምሱ።”

የሚል የጠጅ ቤት ግጥም ጭምር ነበር። አሁን ግን የዐራት ኪሎ ጠበል ነጥፏል። ባንድ ወቅት አዲሳባ ተቀምጫለሁ። አዲሳባን ለማወቅ ዘወር ዘወር ማለቴም አልቀረም። በተለይ ጠጅ ቤት ጎራ ብዬ አውቃለሁ። የጠጅ ነገር ሕልም ነው። ከአዲሳባ የጎንደር ጠጅ ቤት ይሻላል። ጎንደር አበቅ የለሽ የሚወራው ምሥጢር አዲሳባ ላይ የለም። የጎንደር ጠጅ





ቤቶች መፈንቅለ መንግሥት ድረስ የሚደርስ ትኩስ ወሬ ነበራቸው። ጃንሆይ ሊወድቁ ሰሞን ወሬው አበቅየለሽ ጠጅ ቤት በግልጽ ይወራ እንደነበር አንድ የጎንደር ሊቅ አውግተውኛል። የሆነው ሆኖ የሞርካ ጥበብ የስዋሬ እንጂ የጠጅ ቤት ታሪክ አይደለም። በደንብ መዝግበው።” አለ ታሪኩ ወደ ጌርማ ዘወር ብሎ። ገሞራው ግን ቀጠለ። የራሱም ከሸናሻ ጋር የሚየያዝ ታሪክ አለው። ሽናሻ ሳለ ከሞት እንደበት በመላ ተርፏል። ያን ነበር ሊያመጣው የፈለገው።

“በእኛም የቅኔ ቤት ቆይታ የምታውቁት ነገር ነው። ነጭ አብሾ ፍሰጋ የሸናሻን ምድር ያልረገጠ የቅኔ ተማሪ እንደኳላ ቀር ይቆጠር ነበር። ያ መንፈስ አሁንም በየቅኔ ቤቱ አለ። እኔም በዓሥራ ዘጠኝ ዘጠና ስድስት ዓመተ ምሕረት ወደዚህ ስፍራ ነጭ አብሾ ፍለጋ መጥቼ ነበር። ትዝ ይለኛል። በዚያ ዓመት የሸናሻ ልጆች የአብነት ቀለም ለማጥናት ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። ከዚህ ስመጣ ውዳሴ ማርያም ለማስተማር ተቀጠርሁ። የሸናሻ ውሪ ልጆች ከበቡኝ። ቀስ በቀስ ውዳሴ ማርያም አስደገምኋቸው። ቅኔ አስቆጠርኋቸው፡ ፡ ከዚያም ከአሶሳው ጳጳስ ዘንድ ወስጄ ክህነት አሰጠኋቸው። ትልልቆች ካህናት፣ ንዑሳኑ ዲያቆናት ሆነው ቀጠሉ።